የኤም ኢ አር ኤፍ
የኦገስቲን ፕሮግራም
ከቃሉ በመማር እግዚአብሄርን ማየት
ክፍል ሁለት
ወደ ገላትያ ሰዎች

አንብብ

ጠይቅ

ተማር

ገላትያ - አንብብ- ጠይቅ- ተማር
የጥናት መጽሐፍ

ማውጫ **ገጽ**

የምዕራፍ 1 ቅደም ተከተል..... 1
የመክፈቻ ሰላምታ..... 2
ማስጠንቀቂያና ውግዘት 4
ከእግዚአብሄር የተቀበለው የጳውሎስ ወንጌል 5
የምዕራፍ 2 ቅደም ተከተል 8
የጳውሎስ የኢየሩሳሌም ሁለተኛ ጉብኝት 9
የጴጥሮስ የአንጾኪያ የመጀመሪያ ጉብኝት.....12
የምእራፍ 3 ቅደም ተከተል 19
የጳውሎስ መርማሪ ጥያቄዎች 20
ህግና ወንጌል - ርግማንና በረከት 22
ሁሉም በክርስቶስ አንድ ናቸው 28
የምእራፍ 4 ቅደም ተከተል.....30
በወራሾች ህይወት ውስጥ ያሉ ደረጃዎች.....31
የገላትያ ሰዎች ድርጊት አሳዛኝ ሁኔታ 35
ሁለቱ ኪዳኖች.....37
የምዕራፍ 5 ቅደም ተከተል.....41
ህግ ሳይሆን ነጻነት፣ ፈቃድ ሳይሆን ፍቅር..... 42
የተሳተፉ ሰዎችና የተመለሰ ጥያቄ.....43
መንፈስ ስጋ ህግ.....45
የምእራፍ 6 ቅደም ተከተል.....49
የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ህይወት.....50
የትምክህት የተሻለና መጥፎ አይነቶች..... 55
ማጠቃለያ 56

ገላትያ 1

የምዕራፍ 1 ቅደም ተከተል	
1 የመክፈቻ ሰላምታ	ሀ) ጸሐፊውና ስልጣኑ(ቁ 1)
	ለ) ሰላምታ፣ ጸሎት እና የመሰረታዊ እውነታዎች ማስታወሻ (ቁ 2-5)
2 ማንቂያ እና ውግዘቶች	ሐ) የገላትያ ሰዎች በወንጌል ላይ ጀርባቸውን ሲያዞሩ የጳውሎስ ማንቂያ (ቁ6)
	ለ) ሆነ ብሎ ወንጌልን በሚያጣምምና ልዩ 'ወንጌል' በሚሰብክ ላይ የጳውሎስ ውግዘት (ቁ. 7-10)
3የጳውሎስ ወንጌል ከእግዚብሔር ነው! ከየትኛውም ሰው አይደለም!	ሀ) ጳውሎስ ሐዋርያነቱንና መልእክቱን እንዴት እንደተቀበለ (ቁ11-17).
	ለ) መልእክቱንና ስልጣኑን ከሐዋርያት ወይም ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እንዳልተቀበለ ጳወሎስ ግልጽ ያደርጋል) (ቁ 18-24).

1 የመክፈቻ ሰላምታ

1ሀ ጸሐፊውና ስልጣኑ (ቁ1)

1 ገላትያን የጻፈው ማን ነው?

ገላትያን የጻፈው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው 1:1

2 በማን ሥልጣን ነው ደብዳቤውን የጻፈው?

በእግዚአብሄርና በኢየሱስ ክርስቶስ ስልጣን ነው እንጂ በሰዎች ሥልጣን አይደለም የጻፈው።

3 ቁ 1 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነግረን 3 ነገሮች ምን ምን ናቸው?

1. ጳውሎስን ሐዋርያ አድርጎ እንደሾመው
2. እንደሞተ
3. በአባቱ ከሙታን እንደተነሳ

4 ጳውሎስ ስሚጽፈው እምነት ብቸኛ ነበርን? (ቁ. 2)

ጳውሎስ በእምነቱ ብቻውን አልበረም፣ ከእርሱ ጋር የነበሩት ክርስቲያን ወንድሞች ሁሉ በሚጽፈው ነገር ይስማማሉ።

1ለ ሰላምታ፣ ጸሎት እና የመሰረታዊ እውነታዎች ማስታወሻ (ቁ 2-3)

5 የገላትያ ሰዎች እነማን ነበሩ?

ጳውሎስ አይነግረንም። ሁለት የሚገመቱ መልሶች አሉ።

i. አንዳንዶች "በሰሜን ገላትያ ይኖሩ የነበሩ የሴልቲክ ሰዎች" የገላትያ ሰዎች ተብለው የሚጠሩ ነበሩ ይላሉ።

ii. ደብዳቤው በደቡብ ገላትያ በመጀመሪያ የአገልግሎት ጉዞው ለመሰረታቸው አብያተ ክርስቲያናት ተጽፎ ሊሆን እንደሚችል ይበልጥ ይታመናል። በጳቄጶድያ፣ አንጾኪያ፣ ኢኮንየም፣ ልስጥራ እና ደርቤ አብያተ ክርስቲያናት።

በሰሜን ገላትያ ምንም የቤተ ክርስቲያን ተከላ ገለጻ የለም። ሐዋ ሥራ 16:6 በደቡብ ገላትያ የሆነ ነው የሚመስለው። በሐዋ ስራ 18:23 ያለው ጉብኝትም ደግሞ ስለነበሩት ደቀ መዛሙርት የሚናገር ነው። ደብዳቤው በደቡብ ገላትያ ላሉ ሰዎች ነው የሚለውን ሃሳብ የሚያጠናክረው የተጻፈላቸው ሰዎች በርናባስን ያውቁት ስነበር ነው (ገላት 2:1፣9 እ 13)።

ደብዳው የተጻፈው መቼ ሊሆን ይችላል?

ጳውሎስ ስለ ኢየሩሳሌም ጉብኝቱ በመሀላ ይጽፋል (ቁ. 20)። በደብዳቤው ውስጥ ሁለት ብቻ ይገልጻል፣ ገላ 1፡16-18 እና 2፡1-5። ይህ ማለት በገላትያ 2 ውስጥ ያለው የኢየሩሳሌም ጉባኤ ስብሰባ አልነበረም ምክንያቱም ያ ለኢየሩሳሌም 3ኛ ጉዞው ምክንያት ነበር።

የመጀመሪያው ጉብኝት ሐዋ ስራ 9፡ 26-30

ሁለተኛው ጉብኝት ሐዋ ስራ 11፡27-30 እና 12፡25

ሶስተኛው ጉብኝት ሐዋ ስራ 15 (የኢየሩሳሌም ጉባኤ)

i. *ስለሁለተኛው ጉብኝት "በራዕይ" እንደሄደ ይናገራል፤ ገላትያ 2፡2። ይህ ከገላትያ 155፡2 ሳይሆን ከሐዋ ስራ 11፡27-30 ጋር ይስማማል*

ii. *ደብዳቤው ከሐዋ ስራ 15 የኢየሩሳሌም ጉባኤ በኋላ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ ከዛ በኋላ ጳውሎስ ሰለርሱ ምንም አለመግለጹ ወይም በግርዘት ጥያቄ ላይ ደብዳቤው ከዛ መላኩን አለመጥቀሱ እንግዳ ነገር ይሆናል ።*

እነዚያ አዋጆች (ሐዋ ሥራ 15፡22-29) እዚህ ለሚጽፋቸው ክርስቲያኖች የሚገጥሙአቸውን አንዳንድ ችግሮች ሊመልሱ ይችሉ ነበር። እነዚያ አዋጆች ቢኖሩ ኖሮ ጳውሎስ ቢያንስ በደብዳቤው ውስጥ ይጠቅሳቸው ነበር።

የገላትያ ደብዳቤ ከኢየሩሳሌም ጉባኤ በፊት እንደተጻፈ መደምደሙ መልካም ነው።

ይሄ ገላያን የጳውሎስ የመጀመሪያ ደብዳቤ ያደርገዋል ፣ " በ49ኛቹ መጀመሪያዎች ላይ ተጽፎ ሊሆን ይችላል" (ዴሪክ ቶማስ - ገላትያን እናጥና - የእውነት ባንዲራ)

6) ቁ 3 "ስለ ጸጋና ሰላም" ምን ይነግረናል?

ጸጋና ሰላም ከእግዚአብሄር አብና ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጡ ስጦታዎች ናቸው። በክርስቲያን ልቦች እንደሚገቡ ዘወትር እንደሚፈሱ የበረከት ምንጮች ናቸው።

ጸጋ የእግዚአብሄር ያልተገባ ፍቅር ወደ እኛ መድረስ ነው።

ለእኛ የእግዚአብሄር የደህንነት ስጦታ ለእኛ መፍሰስ ነው፣ አጽናኝ፣ ዋስትና ሰጪ፣ በሀጢአት ላይ ሀይልን የሚሰጠን እና ክርስቶስን እንድናገለግል የሚያስችለን ነው።

ሰላም የይቅርታ ደስታ እና በሁሉም የደህንነት በረከቶች መደሰት ነው።

7. ቁ 4-5 ስለ ኢየሱስ እና ስለ እግዚአብሄር አብ ምን ይነግሩናል?

- *ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ራሱን ፈቅዶ መስጠቱን*
- *በሀጢአታችንና በአሁኑ ክፉ አለም ተጠምደን ራሳችንን ማዳን አለመቻላችንን*

- *እግዚአብሄር አብ ደህንነታችን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዳቀደውና ሁሉም እንደርሱ ፈቃድ እንደሆነ*
- *ደህንነታችንን በተመለከተ ከዘላለም እስከዘላለም ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር መሰጠት እንዳለበት*
- *ለደህንነቱ ማንም ሰው የሆነ ነገር እንዳዋጣ ሆኖ መመካት በፍጹም እንደሌለበት ይነግሩናል።*

2. ማንቂያና ውግዘት ገላትያ 1 ቁ 6-10

2ሀ ገላትያ ሰዎች ጀርባው በወንጌል ላይ ሲያዞሩ የጳውስ ማንቂያ

8. ጳውሎስን ያስደነገጡት ሶስት ነገሮች ምን ነበሩ (ቁ 6)?

የገላትያ ሰዎችን በተመለከተ ጳውሎስ ሶስት ነገሮች አስደንግጠውት ነበር፡-

i. በክርስቶስ ወደ ደህንነት ከጠራቸው ከእግዚአብሔር እየራቁ የነበር መሆኑ

ii. በክርስቶስ ከእግዚአብሄር ጸጋ መቀበል ወደ ልዩ ወንጌል ዘወር እያሉ የነበር መሆኑ

iii. የወንጌልን በረከት ካመኑና ከተለማመዱ በኋላ ይህን ያደረጉት በቶሎ መሆኑ

9. ከዚህ አዲስ አማኞች ስሚያስፈልጋቸው ጥንቃቄ ምን እንማራለን?

አዲስ አማኞች ከስህተት አስተማሪዎች እና ከክርስቶስ ከሚያርቋቸው **መጠበቅ** *ያስፈልጋቸዋል።*

በወንጌል እውነታዎች በሚገባ መተከል አለባቸው የስህተትን ትምህርት ለይተው ማወቅ እንዲችሉ።

2ለ. ሆነ ብሎ ወንጌልን በሚያጣምም እና ሌላ ወንጌለን በሚሰብክ ሰው ሁሉ ላይ የጳውሎስ ቁጣ (ቁ. 7-10)

ቁ 7ን አንብብ፡

የተጣመመ ወንጌል ልዩ ወንጌል ነው

ደግሞም በፍጹም ወንጌል አይደለም

የትኛውንም እና ሁሉንም የእውነት ወንጌል መጣመም እንዲሁም ልዩ ወንጌል መስበክን

ጳውሎስ በቁጣ ያወግዛል (ቁ 8-9)፡፡

ለወንጌልን እውነት፣ ለእርሱ መጣመም እና ከርሱ ማፈንገጥ በትክክል ዋጋ እንደምንሰጥ ታስባለህን?

10. የወንጌልን እውነተ መመከት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

የወንጌልን እውነት መመከት አስፈላጊ ነው ምንያቱም የእግዚአብሄር ክብርና ምስጋና በእውነተኛ ወንጌል ብቻ ነው መታወቅ የተቻለው፡፡

የነፍሳት የአሁን መዳንናና ዘላለማዊ ፍጻሜ እነርሱን በመስማት ላይና ክርስቶስን በመስማት የተመሰረተ ስለሆነም ደግሞ አስፈላጊ ነው፡፡

11. የወንጌል ሰባኪዎች ሁለቱንም፣ ሰዎችንም እግዚአብርንም አሰደሳች ልምን አይሆኑም? (ቁ. 10)

የእግዚአብሄር ጸጋ ወንጌል የሰውን ሀይል አልባነትና ትምክህት በሀይል ይመታል፡፡ ዝቅ የሚያደርገን መልእክት ነው፡፡ ሀጢአተኝነታችንን እና አቅም የለሽነታችንን ይነግረናል፡፡ ደግሞም በጸጋ ብቻ ነው መዳን የቻልነው፡፡

ሰውን አስደሳች ወንጌል ሰው ያን ያክል መጥፎ እንዳልሆነ ይግረዋል ደግሞም ደህንንቱን እንደሚገባው ወይም መስራት እንደሚችል ወደማሰብ ሊሄድ ይችላል፡፡

እግዚአብሔርን የሚያከብር ወንጌል፣ ብቸኛው ወንጌል፣ ስለሰው መዳን ሁሉን ክብር ለእግዚአብሔር ይሰጣል፡፡

ደህንነት በጸጋ ብቻ ነው፡፡

3.የጳውሎስ ወንጌል የመጣው ከእግዚአብሔር ነው! ከማንም ሰው አልጣም!

3ሀ. ጳውሎስ እንዴት ነው ሐዋርያነቱንና መልእክቱን የተቀበለው?

12 ከቁ 11-12፣ ወንጌል የማን የምስራች ነው?

በርግጥ የሰው ወንጌል አልነበረም፡፡ የእግዚአብሄር ወንጌል ነበር ደግሞም ነው፡፡

13 ጳውሎስ እንዴት ይህ የምስራች ሊኖረው ቻለ?

በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሄር ዘንድ በመገለጥ ወደ እርሱ መጣ፡፡ ከማንም ዘንድ ወደርሱ አልመጣም ደግሞም በክርስቲያን አስተማሪዎች የተማረው ነገርም አልነበረም፡፡

3ለ መልእክቱን ወይም ስልጣኑን ከሐዋርያት ወይም ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እዳልተቀበለ ጳውሎስ ግልጽ ያደርጋል፡፡

14 ጳውሎስ ለምንድን ነው ሀ) ለአይሁድ ሀይማኖት እንዴት ይቀና እንደነበር እና ለ)እርሱን ከሌሎች አብልጦ ያደርግ እንደነበር የሚጽፈው (ቁ 13-14) ?

አንባቢዎቹ አሁን በእነርሱ መካከል ይሁዲነትን እያስተማሩ ባሉት ሰዎች ላይ ሲጽፍ ምን እየተናገረ እንደሆነ እንዲረዱ ፈልጓል።

ስለ ይሁዲነት ያለው እውቀት ከትችት የተነሳ አይደለም ከራሱ ልምድ ተነስቶ ነው የሚያውቀው። ለነገሩ በአይሁድ ሀይማኖት ሊቅ ነው።

5.ከቁ 15-17 ውስጥ የጳውሎስ ስራና መልእክት ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር መሆናቸውን የሚያሳዩ አራት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

1. እግዚአብሄር ገና ሳይወለድ ለስራ አስቀድሞ መርጦታል

2. እግዚአብሄር በጸጋው ለደህንነት እና ለዚህ ስራ ጠርቶታል

3. ስለ ልጁ መስበክ ያለበትን ነገር ሁሉ እግዚአብሄር ግልጦለታል

4. ስለ መልእክቱ ጳውሎስ ለማንም አልተናገረም

በውይይት የተገኘ አልበረም። ወዲያውኑ ከሌሎቹ ሐዋርያት ጋር አላዳበረውም ግን በቀጥታ ወደ አረቢያ ነበር የሄደው።

16. ለምንድን ነው ጳውሎስ ወንጌሉን የተቀበለው ከሌሎቹ ሐዋርያት ጋር ሳይሆን እንደሆነ ለመናገር ያሰበው (ቀ. 16-17) ?

መልእክቱን የተቀበለው በቀጥታ ከእግዚአብሄር እነደሆነ ፍጹም ግልጽነት እንዲኖረው ፈልጓል።

የመስበክ መልእክቱና ስልጣኑ ከእግዚአብሔር ነው የመጣው።

ያን መለኮታዊ ተልእኮ ከእርሱ ማንም አልወሰደውም።

በኢየሩሳሌም ያሉት ሐዋርያት የመስበክ ስልጣኑን መከልከል አይችሉም ነበር ምንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ እነርሱ አልሰጡትም ነበር።

17 ለጊዜአትና ከኢየሩሳሌም መሪዎች ጋር ላለው ለተገደበ ግንኙነት ጳውሎስ አጽኖት መስጠት የሚሞክረው ለምንድን ነው?

ገና ከሐዋርያት አንዱንም ከማግኘቱ በጣም አስቀድሞ ጳውሎስ የሚሰብከውን ወንጌል በሚገባ እንደሚያውቀው ግልጽ እያደረገ ነበር። ከእግዚአብሄር ራዕይ የተቀበለባቸው ሶስት አመታት ልክ ደቀመዛሙርቱ በምድር በነበረበት ጊዜ ከጌታ ጋር እንዳሳለፉት ሶስት አመታት ያሉ አመታት ነበሩ።

ከሐዋርያው ጴጥሮስ ጋር በኢየሩሳሌም የ15 ቀናት ጉብኝቱ በአረቢያና በደማስቆ ከጌታ ጋር የነበረውን ሶስት አመታት አያፈርሰውም። ወንጌሉና ስልጠናው ከእግዚአብሄር ዘንድ ነበሩ።

18. ከቁ 21-23 በሲርያ እና በኪልቂያ ጳውሎስ ምንድን ነው እያደረገ የነበረው?

ጳውሎስ አንድ ጊዜ ሊያጠፋው ሲሞክር የነበረውን ወንጌል እየሰበከ ነበር ።

19 ስለ ወንጌሉ ይኖሩ ከነበሩት ክርስቲያኖች ጳውሎስ ስለ ወንጌሉ ይዘት ምንም እዳ አልነበረበትም። ይህ ማለት የእርሱ ክርስትና የተለየ ክርስትና ነው ማለት አይደለም።

ከቁ 22-24 የእርሱ ወንጌል ከእርሱ በፊት በይሁዳ ቤ/ክ ባሉት ሁሉ ይሰበክና ይደረግ ከነበረው ወንጌል እና ክርስትና ጋር ተመሳሳይ እንደነበር አመላካች የሆኑ 3 ነገሮች ምን ምን ናቸው ?

1) *ጳውሎስ እንደተከላቸው በይሁዳ ያሉትም አብያተ ክርስቲያናት "በክርስቶስ" ነበሩ። "በክርስቶስ" እንደሆኑ ነው ጳውሎስ ስለ ሁሉም ክርስቲያኖች የተናገረው፣ ።*
2) *በይሁዳ ያሉ ክርስቲያኖች ያንኑ ያመኑትን ወንጌል ጳውሎስ እየሰበከ እንደነበር አውቀዋል። አንድ ወቅት ላይ ሊያጠፋው ሲሞክር የነበረውን ወንጌል።*
3) *በይሁዳ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ሁሉም ጳውሎስ ያደርገው በነበረው ነገር እግዚአብሄርን አከበሩ። ልዩ ወንጌል እየሰበከ እንደሆነ ቢያስቡ ኖሮ ያንን አያደርጉም ነበር።*

ገላትያ 2

የምዕራፍ 2 ቅደም ተከተል	
1 የጳውሎስ የኢየሰሩሳሌም ሁለተኛ ጉብኝት	ሀ) ቁ. 1 - 5 ቲቶ መገረዝ እንዳለበት ሲገፋፉ በነበሩ ሰላዮች የተቋረጠ የግል መገናኘት፡፡ የወንጌልን እውነተ በመመከት ጳውሎስ ይህንን ማድረግን በፍጹም ተቃወመ፡፡
	ሐ) ቁ 6-10 የግል መገናኘቱ ለብቻ ቀጠለ፡፡ የኢየሩሳሌም አእማድ መሪዎች የጳውሎስን መልእክት ይዘት ደግሞም በአህዛብ መካከል እግዚአብሄር እርሱን እንዴት እየተጠቀመበት እንዳ ሰሙ፡ ፡ ቀኝ እጃቸውን ለጳውሎስ በመዘርጋት መተባበራቸውን አሳዩ ስለዚህም ለስብከቱና ለተልእኮው እውቅና ሰጡ፡፡
2 የጴጥሮስ የአንጾኪያ የመጀመሪያ ጉብኝት	ሀ) ቁ. 11-13 “በግርዛት ቡድን” ተጽኖ ስር ሲደረግ የጴጥሮስ ወጥ ያልሆነ ጠባይ ፡፡ የዚህ ውጤት በሌሎች ላይ፡፡
	ለ) ቁ 14 ለዚህ የጴጥሮስ አደባባይ ስህተት የጳውሎስ አደባባይ ተግሳጽ
	ሐ) ቁ 15-21 የጳውሎስ ጽድቅ በእምነት ብቻ ነው የሚል ጽኑ መከላከል፡፡ ሀጢአት ለማድረግ ፈቃድ ይሰጣል ለሚል ላልተነገረ ግን ለነበረ ለዚህ ዶክትሪን ትችት የተሰጠ የጳውሎስ መልስ፡፡

1. የጳውሎስ የኢየሩሳሌም ሁለተኛ ጉብኝት

1ሀ. በሰላዮች የተቋረጠ የግል መገናኘት

1. ይህ ጉብኝት ስለተካሄደበት ጊዜ ሁለት ዋና ዋና አስተያየቶች አሉ። የሐዋ ስራ 11 ወይም የሐዋ ስራ 15 ጉብኝት።

የበለጠ ልክ የሚመስልዉ የትኛው ነው?

የሐዋ ሥራ 11፡27-30 ይበልጥ ትክክል ይመስላል።

i. ቁ 2 ላይ ጳውሎስ "በራዕይ ወደ ላይ እንደሄደ" ይናገራል ይህ ደግሞ ከሐዋ ስራ 11፡27-28 ጋር ይስማማል

ii. የዚያ ጉብኝት አላማ ጳውሎስ "ማድረግ የሚወደው እንደሆነ የሚናገረው" የድሆች መረዳት ነበር። ገላ 2፡10።

iii. በግል ከመሪዎች ጋር እንደተገናኘ ጳውሎስ ይናገራል 2፡2። በሐዋ ስራ 15 ላይ ያለው የኢየሩሳሌም ጉባኤ የግል ስብሰባ አልበረም።

iv. ስብሰባው የሐዋ ስራ 15ቱ ከነበረ ጳውሎስ የራሱን ደብዳቤ መጻፍ አያስፈልገውም ነበር፤ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ደብዳቤ መጠቀም ይችል ነበር (ሐዋ ሥራ 15፡19-29+30 እና 16፡4)። ምንም ስላልገለጸው በቁ 1 የገለጸው ጉብኝት የሐዋ ሥራ 11 ጉብኝትን ነው፡ ማለቱ መልካም ነው።

2. ከቅዱሳት መጻህፍት ስለ ቲቶ ማግኘት የምትችለውን ፈልግ

- *ቲቶ 1፡5 ሽማግሌዎችን በመሾም አብያተ ክርስቲያናትን ስርዓት እንዲያሲዝ ጳውሎስ በቀርጤስ ተወው*
- *2 ቆሮ 2፡2-4 እና 12-13 እና 7፡6-16 በጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ተልኮ ነበር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ብርቱ ችግር እንዲፈታ። ነገሮች እንዴት እንደተለወጡ በደስታ ለጳውሎስ ሪፖርት ማቅረብ ችሎ ነበር።*

- *2 ቆሮ 8፡16-24 ቲቶ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተሰጠው እንክብካቤ ነበር ደግሞም ለእርዳታው ስራ ስጦታቸውን ለማስተካከከል እነርሱን ለመጎብኘት ደስተኛ ነበር ። ቲቶ ከሌሎች ጋር በሚገባ ሰርቷል። ከጳውሎስም ጋር ለቆሮንቶሳውያን ጥቅም "አጋርና አብሮ የሚሰራ" ነበር።*

3. በገላትያ 2፡1-10 ምን ያህል ጊዜ ነው ጳውሎስ "ተጽኖ አድራጊ ይመስላል" የሚለውን ቃል የተጠቀመው? ለምን ይመስልሀል እንዲህ ያደረገው?

"ተጽኖ አድራጊ ይመስላል" የሚለውን ቃል 3 ጊዜ ይጠቀማል- አንድ ጊዜ ቁ 2 ላይ ቁ 6 ላይ ደግሞ ሁለት ጊዜ። " ዋና ስለሚመስሉትም " ደግሞ ይናገራል ቁ 9።

እንዲህ ያደረገበት ምክንያት የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡

I. የገላትያ ሰዎች ምን ያህል "ተጽኖ" አላቸው ብለው በሚያስቧቸው ሰዎች ተወስደው እንደነበር ያውቃል ስለዚህም በአስተሳሰብ መንገዳቸው ላይ ጣልቃ ይገባል። የአስተሳሰብ ዘዴአቸውን ስለሚጋራ ሳይሆን እርሱ እያለ ያለውን ነገር መቀበል እንዲችሉ ለመርዳት።

II. ከርሱ ጋር ከሚስማሙ ጥቂት ካልታወቁ ክርስቲያኖች ጋር በኢየሩሳሌም እንዳላወራ ለገላትያ ሰዎች ለማሳየት። አላወራም! በጣም ዋና ከሚባሉ ክርስቲያኖች ፣ በጣም ተጽኖ ካላቸው ሰዎች ጋር፣ ስራቸው ወንጌልን ከሀሰት አስተማሪዎች መጠበቅ ከሆኑ ሰዎች ጋር ነው የተነጋገረው ።

4. ቁ 2ን አንብብ በተለይም የመጨረሻውን ክፍል።

ካለፈው ምዕራፍ ስለሰበከው ወንጌል ጳውሎስ የሆነ ጥርጥር እንዳለው ታስባህን?

የለውም፣ የእርሱ ወንጌል ከእግዚአብሔር እንደሆነ እና የትኛውም ሌላ ወንጌል ሀሰት እንደሆነ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነበር።

በቁ 2 ላይ " በከንቱ እየሮጥኩ እንዳልነበረና እንዳልሮጥኩ እርግጠኛ ለመሆን" ሲል ምን ማለቱ ይሆን?

ይህ ተቺዎቹን ዝም የማሰኘትና አገልግሎቱን የማረጋገጫ ዘዴው ነበር።

እርሱ ምንም እንኳን እውነተኛውን ወንጌል እየሰበከ እንደሆነ እርግጠኛ ቢሆንም በመልእክቱ ላይ ጥርጥር ያላቸው ሌሎች እንደነበሩ ያውቅ ነበረ።

እነዚህ ሰዎች ምናልባት በኢየሩሳሌም ያሉት ሐዋርያት ምን እየሰበከ እንዳለ ቢያውቁ ኖሮ ገና ከብዙ ጊዜ በፊት ያስቆሙት እንደነበርና ለአለፉት አስራ አመታት ዝም እንደማይሉት አስተያየት እየሰጡ ሊሆን ይችላል።

ስብከቱ ሐዋርያዊ እንደሆነ ለእያንዳንዱ ሰው "ለማረጋገጥ"" ፣ የመልእክቱን ትክክለኛነት ለማስረገጥ እና ተቺዎቹን ዝም ለማሰኘት፣ አዲስ የለወጣቸውን ለማበረታታት በኢየሩሳሌም ወዳሉት ወደ ሐዋርያት ለመሄድ አልፈራም

(የማቴዎስ ሄንሪ ማብራሪያ አጋዥ ነው። ከአንላይን መነበብ ይችላል።)

5) ጳውሎስ ሆነ ብሎ ቲቶን ከእርሱ ጋር የወሰደው ለምን ይመስልሃል?

ጳውሰሎ ቲቶን ከእርሱ ጋር ሆን ብሎ ወስዶታል ምክንያቱም የአህዛብ አማኞችን አይገርዝም ተብሎ ችግር እንደሚፈጠርበት ስሚያውቅ ነው።

በስበኩቱ ላይ ትልቅ ተቃርኖና ዋና ክርክር ነበር።

ቲቶን እንደ ማረጋገጫ እና ምሳሌ አደረገው።

ቲቶ መንፈሳዊ ሰው ነበር፣ ማንም ያንን ጥያቄ ውስጥ አያስገባም። ብርቱ ሰውም ነበር ስለዚህ ጳውሎስ በጠበቀው አደጋ ውስጥ ጸንቶ ቆመ።

6. በስበሰባው ላይ ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው የጳውሎስ ትኩረት የነበረው?

የግል ጦርነትን ማሸነፍ?

"ተሰሚነት"" ያላቸውን ሰዎች ማሸነፍ?

ወንጌልን ማቆየት?

አይሁዶችን ማጥፋት?

የጳውሎስ ብቸኛው ጭንቀት የወንጌልን እውነት ማቆየት ነበር፣ ቁ 5።

7. ጳውሎስ የሆነ ጊዜ ላይ ቤተ ክርስቲያንንና ወንጌልን ማጥፋት የሚፈልግ አሳዳጅ ነበር። ቤተ ክርቲያንንና ወንጌልን ለማጥፋት ሰይንጣን አሁን ምን አይነት ዘዴዎችን ነው የሚጠቀመው ?

ሰይጣን ፈጽሞ ክርስቲያኖች ሳይሆኑ ክርስቲያኖች እንደሆኑ የሚያስመስሉ ሰዎችን ይጠቀም ነበር ቤተ ክርስቲያንን ለመበረዝ (ዘልቆ ለመግባት)፣ ቁ 4። እነዚህ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን የሐሰት ወንጌል እንድተከተል ጫና ያርጋሉ። ቤተ ክርስቲያን ለእነርሱ ከተገዛች ሰይጣን ትልቅ ድል ያገኛል።

1ለ. በግል የተደረገው ስብሰባ ቀጥሏል

8. ጳውሎስ እንዴት ነው "የሰው ክብርን/ ፕረሰናሊቲ ከልቶችን " የሚያየው ? እኛስ እንዴት ነው የምንመለከታቸው? (1 ቆሮ 3፡1-4ንም ይመ)

ፕርሰናሊቲ ከልቶችን ጳውሎስ ሐሰት፣ ሰው ሰራሽ የስልጣንና የተጽኖ ሀይሎች አድርጎ ነው የሚያያቸው።

በእነርሱ መያዝን አይፈልግም።

እኛም በእነርሱ መያዝ የለብንም። ቤተ ክርስቲያንና የክርስትና እምነት ስለ ሰዎች ስልጣን አይደለም ስለ ክርስቶስ ክብር ኢየሱ ብቻ ነው። (ዮሐ 3:30)።

9. ጳውሎስ የሚፈልገው ነገር ምን ነበር (ቁ 8) ?

1 ቆሮ 3፡10

1 ቆሮ 4፡ 1 እና 6-7

1 ቆሮ 15፡10ንም ይመልከቱ።

ማንም ያድርገው ጳውሎስ በወንጌል ስራ መሳካት ደስተኛ ነበር።

ማንም ምንም ቢሰራ ለእርሱ ምንም ጉዳይ አይሰጠውም ነበር፤ የሆነ ሰው ሊተክል ይችላል ሌላው ደግሞ ሊያጠጣ፣ የሆነ ሰው መሠረት ሊጥል ሌላው ደግሞ በርሱ ላይ ሊሰራ። ግድ የሚለው ነገር ሁሉም በእግዚአብሔር ጸጋ መደረጉ እና ሰዎች መዳናቸውና በእምነት ማደጋቸው ነበር።

1ለ. በኢየሩሳሌም የግል ስብሰባው ቀጥሎአል፡

10. በኢየሩሳሌም ያሉት መሪዎች ለመልእክቱ "ምንም እንዳልጨመሩ" ከርሱም ምንም እንዳልቀነሱ ጳውሎስ ግልጽ ያደርጋል ቁ. 6)።

"የመገረዝን ቡድንን" ክሌይም ሰጥ የሚያደርግ ምን ነገር አደረጉ?

ቁ 3 ላይ ቲቶ እንዳይገረዝ ከለከሉ ለጳውሎስና ለበርናባስ "የመተባበር ቀኝ እጃቸውን" ሰጡአቸው ቁ 9

2. የጴጥሮስ የአንጾኪያ የመጀመሪያ ጉብኝት

ይህ ጉብኝት ለጳውሎስ ""የመተባበር ቀኝ እጅ" መስጠት ተግባራዊ መግለጫ ነበር ። ያረጋገጠው ግን ተቃራኒውን ነበር።

2ሀ. የጴጥሮስ ወጥነት የሌለው ባህሪ ቁ 11-13

11. ጴጥሮስን ከአህዛብ ጋር እንዲበላ ያደረገው ነገር ምንድን ነው (ሐዋ ሥራ 10፡1-11፡18) ?

በእንስሳት የተሞላ ሸማ በራዕይ እግዚአብሄር አሳየው። ከጴጥሮስ የይሁዲነት ታሪካዊ ዳራ አነጻር ንጹህ ያልሆኑ እንስሳት ነበሩ። እግዚአብሄር በነገረው ራዕይ ውስጥ (እንዲነሳና አርዶ እንዲበላ" ነገረው። ጴጥሮስ ተቃወመ ጌታ ግን "እግዚአብሄር የቀደሰውን ርኩስ ነው አትበል" አለው። ይህ ራዕይ ከቆርነሌዎስ ቤት ለሚመጡ ሰዎች አዘጋጀው። ከቆርነሌዎስ ቤት የመጡ ጎብኚዎች ከነርሱ ጋር ወዳህዛብ ቤት እንዲሄድ ጠየቁት። በእግዚአብሄር ትዕዛዝ ሄደ። ወደ

አህዛብ ቤት ገባ፣ ለእርሱና በዚያ ለተሰበሰቡ ሁሉ ወንጌል ሰበከ። ተለውጠውና በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው አያቸው። ደግሞም እግዚአብሄር አህዛብን ወደ ህዝቡ ቤተሰብነት እንዳመጣቸውም ተረዳ። ለበርካታም ቀን ከነርሱ ጋር ቆየ። ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ እግዚአብሄርን ባመኑ ጊዜ ለአህዛብ ተመሳሳይ ስጦታ እንደተሰጠ በማስረዳት ያደረገውን ነገር ተከላከለ። በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን ደህንነት እንዲካፈሉ ለአይሁድና ለአህዛብ በግልጽ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነበር ።

12. የጴጥሮስ ከአህዛብ ጋር ከመብላት ሀሳብ መወሰድ በአብያተ ክርስቲያኖች ውስጥ ስላለው የተጽኖ ሃይል ምን ይነግረናል?

በቤተ ክርስቲያን ያሉ አንዳንድ ሰዎች አንድም ቃል እንኳን ሳይተነፍሱ በሌሎች ላይ በጣም ጠንካራ ተጽኖ እንዳላቸው ያሳየናል።

የነርሱ መኖር ወይም የነርሱ አቋምና የቆሙለት ነገር ሰዎችን ለነርሱ ለማንበርከክ በቂ ነው። ደፋሩና ብርቱው ጴጥሮስ ለእንደዚህ ያለ ግፊት መስገድ ከቻለ፣ በእኛ ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ያሉ ሌሎች ክርስቲያኖች እንዴት በቀላሉ ጠንካራ ስእብዕናን በተሳሳተ አቅጣጫ ለመከተል ተጽኖ ስር አይወድቁም።

የእግዚአብሄር መንጋ ከአስጫናቂ በጎች መጠበቅ አለበት (ሕዝ 34፡17-24)።

13. የጴጥሮስ ድካም በሌሎች ላይ ካመጣው ተጽኖ ምን እንማራለን (ቁ 13) ?

በጣም የተከበሩ ክርስቲያኖች ስህተትን ሲሰሩ በጣም ጠንካራ ያልሆኑ ሌሎች ክርስቲያኖች ምሳሌአቸውን እደሚከተሉ እናያለን።

ከዚህ የምንማረው ሌሎች አማኞች እንደምሳሌ ለሚያዩአቸው ክርስቲያኖች የሚሰጡት ምሳሌ መልካም መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። ወላጆች፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች እና የወጣት ሰራተኞች ስለሚሰጡትን ምሳሌ መጠንቀቅ አላቸው።

በወንጌል ላይ ተቃራኒ በማይሆን መንገድ መኖር አለባቸው (ሮሜ 14፡13፡15፡7)

14. ቁ. 13 ላይ "በግብዝት" ማለት ምን ማለት ነው?

እዚህ ላይ "በግብዝነት" ማለት "ለእውነተኛ መረዳታቸው ጋር የሚቃረን ነገር ማድረግ ማለት ነው።"

2ለ በቁ 14 ላይ ለዚህ የጴጥሮስ አደባባይ ስህተት የጳውሎስ የአደባባይ ተግሳጽ

15. በመሠረቱ እንዴት ነበር ጴጥሮስ እንደ አህዛብ ይኖር የነበረው (ቁ 14) ደግሞስ እንዴት ነው አህዛብን እንደ አይሁድ እንዲኖሩ አሁን የሚያስገድዳቸው?

አሁን ክርስቲያን እንደመሆኑ የጴጥሮስ የዘወትር የህይወት ዘይቤ የአይሁድን ህግ ያለመከተል እንደኖሩት ልክ እንደ አህዛብ ነበር።

ገበታን በመቀየር ክርስቲያን እንዳልሆኑት አይሁድ እንዲኖሩ ተነግሮአቸው የነበሩትን አህዛብን በአይሁድ ህግ እንዲኖሩ እያስገደደ ነበር።

2ሐ. እምነት በጽድቅ የሚለው የጳውሎስ እጅግ አስፈላጊ መከላከያ

16. በቁ. 15 ላይ ጳውሎስ "አህዛብ ሀጢአተኛ ሆነው ተወልደዋል፣ እኛ አይሁድ እንደዛ ሆነን አልተወለድንም የሚል ይመስላል"

አይሁድ ልክ እንደ አህዛብ በሀጢአት አልተወለዱም ማለቱ እንዳልሆነ እንዴት እናውቃለን?

ሀ) ቁ 16ን ተመልከት

ከዚህ ክፍል ጳውሎስ አይሁድም አህዛብም በሀጢአት እንደተወለዱ ማወቁን እንረዳለን።

በቁ 16 አይሁድ በእግዚአብሄር ፊት ትክክል መሆን (መጽደቅ) እንዳለባቸው ያውቃሉ ብሎ ይናገራል። መጽደቅ የሚያስፈለጋቸው ሀጢአተኞች መሆናቸውን ያውቁ ነበር። ደግሞም የእግዚአብሔርን ህግ ለመታዘዝ በመሞከር ጽድቅን ማግኘት እንዳልቻሉም ያውቁ ነበር።

ለ) ሮሜ 1-3ን ተመልከት (3:9፣23)

በሮሜ 1-3 ወንጌል ለአይሁድና ለአህዛብ እንደሆነ ይናገራል (1:16)። አይሁድ ከአህዛብ ያልተሻሉ እንደሆኑም ያስረዳል ምክንያቱም ሁሉም ከሀጢአት በታች ስለሆኑ (3:9)።

ስለዚህ ምንም ጥርጥር እንደሌለ በሮሜ 3:23 "ሁሉም ሀጢአትን ሰርተዋል የእግዚአብሄርም ክብር ጎድሎአቸዋል" በማለት ይጽፋል።

17. ሀጢአተኛ ሆኖ ስለመወለድ ካልሆነ ጳውሎስ የሚናገረው፣ በአይሁድና በአህዛብ መካከል ምን ልዩነትን ነው የሚያሳላው?

ሀ) ቁ 14 ለ እና 16ን ተመልከት

ለ) ሮሜ 3:1-2፣ 7:7ን ተመልከት

ሐ) ገላትያ 1:4፣ ፊሊ 3:6፣ ሉቃስ 1:6ን ተመልከት

ጳውሎስ የሚያሳየው ዋና ልዩነት አህዛብ ክርስቶስ እስኪመጣ እደሞግዚት ህጉን በመስጠት እንደባረካቸው ነው። (ገላ 3:23-24)።

አይሁድ ህይወታቸውን ለመምራት የእግዚአብሔር አስደናቂ ህግ ወዳለው ህዝብ ተወልደዋል (ቁ 14፣ አይሁድ ከህግ በታች ይኖራሉ፣ አህዛብ ይህ የላቸውም።)

18. አይሁድ ሆኖ በመወለድ እና ከህግ በታች ሆኖ በመወለድ፣ ጳውሎስ፣ ጴጥሮስ እና ሌሎች እውነተኛ አይሁድ በአንጾኪያ የሚያውቁት ነገር ምን ነበር (ቁ 16) ?

በዚያ ያለ ማኛውም ትክክለኛ አይሁድ በህግ እንደማይጸድቅ እና ሌላ የመጽደቂያ መንገድ እንደሚያስፈልግ ያወቀ መሆን አለበት (ቁ16)

19. ቁ 16 ላይ "መጽደቅ" ማለት ምን ማለት ነው?

በቁ 16 ላይ መጽደቅ ማለት፡

በእግዚአብር ጻድቅ ሆኖ መቆጠር እና መታየት ነው።።

የሀጢአታችን ሁሉ ይቅር መባል እና ልክ ሁሉንም የእግዚአብሄር ህግ የሚጠይቀውን ሙሉ በሙሉ እንደፈጸምን መቆጠር ነው።። በእግዚአብሄር ሙሉ በሙሉ ጻድቅ ሆኖ መታየት ነው።።

የሀጢአት መዝገባችን ሙሉ በሙሉ መታጠብና ነጻ መሆን የጽድቅ መዝገባችን ፍጹም ሙሉ መደረግ ማለት ነው።።

"በፍጹም ሀጢአት ሰርቼ እንደማላውቅ" እና በእግዚአብሄር ህግ መሰረት "ሁሉንም ነገር በትክክል እንዳደረኩ" መሆን ማለት ነው።።

(የዌስት ሚኒስቴር አጭር ካታኪዝም ቁጥር 33 በጣም አጋዥ ነው፡

"ጽድቅ ምንድን ነው?

መልስ፡ "ጽድቅ ሀጢአታችንን ሁሉ ይቅር የሚልበትና በእርሱ እይታ ጻድቅ አድርጎ የሚቀበልበት የእግዚአብሄር ነጻ ጸጋ ክንውን ነው።። የክርስቶስ ጽድቅ ብቻ ተቆጥሮልናል በእምነት ብቻ ተቀብለናልና")

20. ቁ 16 "የህግ ስራ" ማለት ምን ማለት ነው?

"የህግ ስራ" ማለት እግዚአብሄር በህጉ ውስጥ የሰጠውን ትዕዛዝ ሁሉ የእኛ የመጠበቅ ሙከራ ማለት ነው።።

21. ቁ 16 ላይ "እምነት" ማለት ምን ማለት ነው?

"እምነት" ማለት ማመንና መታመን ማለት ነው።። እምነት ስለ ጌታ ኢየሱስ እውነታ ማመን ሲሆን ማመን ስለ ደህንነታችን በሰራው ስራ መታመን ማለት ነው።።

ስለደህንነታችን መተማመናችንን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማኖር ማለት ነው።።

22. በጽድቅ ውስጥ የእምነትና የስራ መደባለቅ ሊኖር ይችላልን?

አይኖርም።። የእምነት (በኢየሱስ ማመንና መታመን) እና "የህግ ስራ" ቅልቅል የለም።።

ጳውሎስ "በስራ አልጸደቅንም" ብሎ ሲጽፍ በርግጥም በእግዚአብሄር ፊት በመጽድቃችን ውስጥ ምንም ሚና የላቸውም ማለቱ ነው።።

ጴጥሮስና ጳውሎስ አይሁዳዊ ሆነው እንደማደጋቸው የእግዚአብሄርን ህግ በመጠበቅ በፍጹም እንደማይጸድቁ ያውቃሉ። ሁለቱም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ መጽደቅ እንደቻሉ ተገንዝበዋል። ስለዚህ አመኑ ጸደቁም።

ላልተነገረው ትችት መልስ መስጠት

ጽድቅ በእምነት ነው የሚለው በተሰበከ ጊዜ ሁሉ፣ እንዲህ ያለ ትምህርት ሁለት ነገሮችን ማድረጉን ይቃወማሉ፡

1) **የሰውን ጥረት መልካምና ቅዱስ ያደርጋል**
2) **ሰዎች ሀጢአትን እንዲያደርጉ ያበረታታል**

ሮሜ 6፡1፣ 15 እና ሮሜ 3፡8ን ተመልከት

"ከያዕቆብ የተላኩ ሰዎች" ወደ አንጾኪያ (ቁ 12) ሲመጡ ጳውሎስ መዋጋት የነበረበት ይህ እንዳልነበረ ምንም ጥርጥር የለውም። ቁ 17።

በክርስቶስ አይሁድም አህዛብም የለም - ሁሉም

አዲስ ፍጥረት ነው - 2 ቆሮ 5፡17፤

ቆላ 3፡9-11፤ ገላ 5፡6፤ 6፡15

23. ቁ 17 ላይ ጳውሎስ "እኛም ሀጢአተኞች ነበርን" ሲል ምን ማለቱ ነው? (ከቁ 15 ጋር አገናኘው) (መልሱ እስከ ቁ 24 ይደርሳል)።

ሐረጎቹን ለመረዳት በጥንቃቄና በራሳቸው መቼት ውስጥ ልናነባቸው ይገባል። የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ አለብን፡

ሀ) በትክክል ጳውሎስ የሚለው ምንድን ነው?

ለ) ያንን እንዲል ያደረገው ምንድን ነው?

ሐ) ጳውሎስ ትርጉሙን በሚቀጥሉት ቁጥሮች ውስጥ ይሰጣልን?

ሀ) በትክክል ጳውሎስ የሚለው ምንድን ነው?

በቁ 17 ጳውሎስ "ነገር ግን እኛም ሀጢአተኞች ሆንን ከተገኘን" ("እኛ" አይልም "እኛም" ነው የሚለው።)

ለ) እንዲህ እንዲል ያደረገው ምንድን ነው?

"እኛም" በሚሉት ቃላት የሚያቆራኘው ማንን ነው?

“ እኛም ደግሞ ሀጢአተኞች ሆነን ከተገኘን” የሚሉት ቃላት ወደ ኋላ ከ ቁ 15 ጋር ይገናኛሉ “ ሀጢአተኞች የሆኑ አህዛብ”።

በቁ 17 ላይ፣ ጳውሎስ “ . .. እኛም . . . ሀጢአተኞች እንደ ሆኑ አህዛብ ሆነን ከተገኘን” ይላል። ይህን ሲል “፣ የእግዚአብሄር ህግ ሀይወታቸውን ሳይገዛቸው ሀጢአት ያደረጉ ሰዎች እንዳልተለወጡት አህዛብ ሲኖሩ ተገኙ” ማለቱ ነው።

የወንጌል ተቃዋሚዎችን ያስቆጣቸው ነገር ያለ እግዚአብሄር ህግ አገዛዝ የሀጢአት ሀይወትን መኖር ነበር።

ሐ) ጳውሎስ ትርጉሙን በሚቀጥሉት ቁጥሮች ውስጥ ይገልጣልን? *አዎን ይገልጣል።*

ራሳችን ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነን ከተገኘን፣ ያፈረሰውን እንደ ገና የሚያንጽ፣ የሕግ ተላላፊን ሀይወት የሚያንጽ ይሆናል ቁ 18።

24. ለመጽደቅ በክርስቶስ በመታመን ጳውሎስ ያፈረሰው ነገር ምንድን ነው? ቁ 18

ሀጢአተኛ እንደነበረ ከተቆጠረ የሀጢአትን ሀይወት ስለሚያንጽ ያፈረሰው ነገር ሀጢአትን የሚያገለግል ሀይወትን ነው።

ሀጢአትን የሚያገለግል ሀይወትም ለአይሁድ የተሰጠ ከእግዚአብሄር ህግ በታች የሆነ ሀይወት ነው። ሀጢአትን ማገልገል ህግን ተላላፊ መሆን ነው።

ጳውሎስ ከህግ በታች ጻድቅ ሆኖ ለመኖር ጥረት ቢያደርግም እንኳን ሀጢአትን መከልከል አልቻለም ነገር ግን በሀጢአት ሀይል ሀያው አደረገው እንጂ ሮሜ 7:8-12።

ለደህንነት በክርስቶስ በመታመን ሁሉንም ነገር አፈራረሰው።

በክርስቶስ ከዚህ በኋላ ከሀጢአት በታች ከህግም በታች አይደለም (ሮሜ 6:14)። ልክ ጴጥሮስ እንደሆነው ሁሉ ከአይሁድ ህግ ነጻ ነበር 2:14።

በክርስቶስ ለመጽደቅ በመሻት ጳውሎስ ያፈረሰው ነገር በሀጢአት እና ከእግዚአብሄር ህግ በታች የነበር ሀይወት ነው።

25. ክርስቶስ በሀጢአት የማይኮነን ሆኖ ሳለ ጳውሎስ ሀጢአተኛ መሆኑን የሚያረጋግጠው ለምንድን ነው?

ከሀጢአት ቅጣት፣ ሀይልና ልምምድ ከሚያድነው ከክርስቶስ የራቀ በመሆን ተላላፊ ሆኖ ነበር። እንደ መልካም እረኛ ክርስቶስ ሁልጊዜ “ስለ ስሙ ሲል በጽድቅ መንገድ” ህዝቡን ይመራል። መዝ 23:3

መተላለፍ የክርስቶስ ሳይሆን የጳውሎስ ተግባር ይሆናል።

26. ሀ) ከቁ 18-19 ጳውሎስ ለምንድን ነው ከህግ በታች ህይወትን የመስራት ጉዳይ የሌለው?

አሁን ለህግ የሞተ ስለሆነ ጳውሎስ ህይወትን ከህግ በታች መገንባት የለበትም።

ለ) ለምንድን ነው ጳውሎስ ሀጢአትን የማገልገል አላማ የሌለው? ቁ 19

አሁን ለእግዚአረርሔ ህያው ስለሆነ ጳውሎስአ ሀጢትን የሚያገለግል ህይወትን መገንባት የለበትም።

27. እንዴት ነው ህግ ጳውሎስን ለእርሱ እንዲሞት ያደረገው (ቁ 20 ሀ)?

ጳውሎስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ወደሞቱ እንዲተከተለው ህጉ ይጥይቃል። ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል ስለዚህ በእርሱ ላይ ተቃዋሚ የነበሩ ሁሉም የህግ ጥያቄዎች በክርስቶስ ረክተዋል።

28. እስካሁን ጳውሎስ በደብዳቤው የእግዚአብሄርን ጸጋ የሚሰራ፣ የሚፈስ፣ የእግዚአብሔር የማዳን ፍቅር አድርጎ ይናገራል፤ 1፡3፣ 6 አእና 15።

የህግና የግረዘት ሰዎች የመለኮዊ ፍቅርን "ባዶ"፣ እንደሚያደርጉ፣ እንደሚገድቡት እና እርሱን እንደሚተው እርሱ ግን እንደዛ እንደማያደርግ በግልጽ ይናገራል! 2፡21

ለእኛ በህግ ሳይሆን በጸጋ የተሰጠን ነገር ምንድን ነው? ቁ 21 (የእግዚአብር የማዳን ፍቅር መፍሰስ የሆነው ጸጋ)።

በእግዚአብሄር ጸጋ ለእኛ የተሠጠን ነገር ጽድቅ ነው።

29. የእግዚአብሄ ጸጋ ሁለት አይነት ጽድቅን ይሰጣል፡

i. ሀጢተኞች ሲያጸድቅ እግዚአብሄር የሚያየው የተሟላና ፍጹም ጽድቅን

ii. የጽድቅ ህይወትን እንዲኖር የዳነውን ሀጢአተኛ ጸጋ አቅም ሲሰጠው ያልተሟላ እና በሂደት ላይ ያለ የህይወት ጽድቅን ይሰጣል።

እዚህ ላይ ጳውሎስ በሃሳቡ ውስጥ ያለው የትኛው አይነት ጽድቅ ነው?

ሁለቱም አይነት ጽድቅ በጳውሎስ ሀሳብ ውስጥ አሉ።

በማዳን ጸጋ ውስጥ በአንድነት ይኖራሉ።

ይበልጥ ማለቱ የሆነው (i) ፣ 2፡16-17 ግልጽ እንደሚያደርገው እኛን ያጸደቀን የክርስቶስ ጽድቅ ነው። 2፡19-20 ግልጽ እንደሚያደርገው ከክርስቶስ ጋር የተሰቀለው አሁን የሚኖረው የጽድቅ ህይወት ማለት ነው። በጸጋ የተኖረ ህይወት። ጽድቅ በሙሉ ትርጉሙ በእግዚአብሄር ጸጋ ወደ እኛ መጥቶአል።

30. የክርስቶስ ሞት አላማ ምን ነበር ?

በሀጢአታችን ላይ የእግዚአብርን ህግ ቅጣት ለመሸከም 2፡19-20

የክርስቶስ ሞት አላማ ከሀጢአታችን እና ከአሁኑ ክፉ አለም ነጻ ሊያወጣን ነው 1፡4፡፡

ገላትያ 3

የምዕራፍ 3 ቅደም ተከተል

1 የጳውሎስ መርማሪ ጥያቄዎች	ሀ) የሰሙት ስብከት ቁ 1
	ለ) በልምዳቸው ላይ የተመሠረቱ አምስት ጥያቄዎች ቁ 2-5
	ሐ)እውነተኞቹ የአብርሀም ልጆች እነማን ናቸው? ቁ 6-9
2 ህግና ወንጌል ህግ ለህይወት ምንድን ነው?	ሀ) ህግ እርግማንን ያመጣል፡፡ ወንጌል ብቻ ነው በረከትን የሚያመጣው ቁ
	ለ) ከህጉ በፊት ነው ወንጌሉ ተስፋ የተሰጠው፡፡ ህጉ በርሱ ላይ አልጨመረም ደግሞም ወንጌሉን አልቀየረውም ቁ 15-
	ሐ) ህጉ ለምን ተሠጠ ለምንስ ተወሰደ? ቁ 19-25
3 ሁሉም በክርስቶስ አንድ ናቸው	ሀ) ለሁሉም ክርስቲያኖች እውነተኛ የሆኑ አራት ነገሮች ቁ 26-29: 1) “በክርስቶስ ናቸው” 2) “ክርስቶስን ለብሰውታል” 3) ሁሉም “በክርስቶስ አንድ ናቸው” ደግሞም 4) ሁሉም ክርስቶስ ዘር “ወረሾች”

1. የጳውሎስ መርማሪ ጥያቄዎች

1ሀ. የሰሙት ስብከት ገላ 3፡1

ቁ.1 የገላትያ ሰዎች ስለተለወጡበት የስብከት አይነት ምን ይነግረናል? ደግሞስ ለራሳችን ስብከት ምን መማር እንችላለን?

ሀ) የስብከቱ ይዘት፡

ስብከቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይና በመስቀል ላይ ስለመሰቀሉ ያተኩራል

ለ) የስብከቱ ባህሪ፡

ስለስቅለቱ በመናገር ስብከቱ ግልጽ ነበር ይሽውም የሚያዳምጡት ሰዎች በአይናቸው ፊት ሲከናወን ማየት ችለው ነበር፡፡

ጆን ካልቪን "ይህ ጳውሎስ የሚነግራቸው ነገር ባዶ ዶክትሪን አለመሆኑን ነገር ግን ህያው የክርስቶስ መልክ መገለጫ መሆኑን የሚያሳየውን የትምህርቱን ግልጽነት ነበር፡፡" "ክርስቶስ "እንደተሰቀለ ሆኖ በፊታቸው ተሰሉ የነበር መሆኑን በእምነት አይን ከነበሩና ሰነዱን ካዩ ከሌሎች ይልቅ ይበልጥ እነርሱ በተለየ ሁኔታ ተረድተውት ነበር ::"

"ስብከቱ ምን ያህል ሀይል የተሞላ እንደነበር ለማየት ጳውሎስ ህያው በሆነ መንገድ የክርስቶስን መልክ በመጀመሪያ ለእነርሱ ከታየ ስእል ጋር ያነጻጽረዋል፡፡"

"የወንጌልን አገልግሎት ልክ ባልሆነ መንገድ የሚያስተላልፉ መናገርና ማወጅ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ እንደተሰቀለ እና የደሙ መፍሰስ እንዲሰማቸው ለማድረግ በሰዎች ህሊና ውስጥ ዘልቆ መግባት እንደሆነ ይማሩ፡፡

ይህ ጽሁፍ ወንጌልን በመስበካችን ላይ ምን

ተጽኖ ያደርጋል

1ለ. በልምዳቸው ላይ የተመሠረቱ አምስት ጥያቄዎች

2.የጳውሎስ የመጀመሪያ ጥያቄ፡ በቁ 2 የአንድ ጥያቄ መልስ ብቻ የገላትያ ክርስቲያችን ወደ እውነታ መንገድ ለሚልሳቸው እንደሚገባ ጳውሎስ ያሳስባል፡፡

ሀ)ጥያቄው ምን ነበር?

ጥያቄው "መንፈስ ቅዱስን የተቀበላችት የህግን ስራ በማድረግ ወይስ በእምነት መስማት ነበር" የሚል ነው፡፡

ለ)እንዲህ አስፈላጊ የነበረው ለምንድን ነው?

የክርስትና ህይወት ተስፋ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ሃይል የሚኖር ህይወት ስለሆነ ይህን ያህል አስፈላጊ ነበር፡፡

(ዮሐ 7:37-39፣ 4:14፣ ሐዋ ስራ 1:4፣ 2:32-33 እና 38፣39፣ገላ 3:14፣ 4:4-7)፡፡ ለዚህ ነው መንፈስ ቅዱስን የተቀበልንት መንገድ ለክርስትና ህይወት አስፈላጊ የሆነው፡፡

3.የጳውሎስ 2ኛ እና 3ኛ ጥያቄዎች፤ በቁ 3 ላይ ጳውሎስ እንዴት ያለ ሞኝ ነገር ነው የሚጠይቃቸው; የክርስትና ህይወትን ስመኖር ለእኛ ምን ይነግረናል?

ጳውሎስ የሚጠይቃቸው የሞኝነት ጥያቄ የክርስትና ህይወትን በመንፈስ ቅዱስ ሰማያዊ በረከት ስለመጀመር ነገር ግን ከዚያ በምድራዊ የሰው ጥረት የክርስትና ህይወትን ለመኖር መሞከር ነበር፡፡

የክርስትና ህይወት በመንፈስ ቅዱስ ሃይል መኖር አለበት፡፡ በሰው ጥረት ብቻ ሊኖር አይቻልም፡፡

4.በመከራ ጊዜ (ቁ4) የገላትያ ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ተቀብለዋል (ቁ.2)፡፡ በመከራ ጊዜአት ክርስቲያች ሊኖራቸው የሚገቡ የመንፈስ ቅዱስ ልምምዶች ምን አይነት ናቸው?

ዮሐ 14:18፣23ን ተመልከት፡፡ በመንፈሱ ወደነሱ ሲመጣ ብቻቸውን እንደሆኑ እንዳይሰማቸው የክርስቶስን አብሮነት በተለየ መንገድ ሊያውቁ ይችላሉ፡፡

1 ተሰ 1:6 መንፈስ ቅዱስ ለስብከቱ ሃይልን ፣ በመከራ ውስጥ እንኳን ሆነው ለአማኞች ማረጋገጫን እና ታላቅ ደስታን ይሰጣል፡፡

ሮሜ 5:3-5 ለእነርሱ ያለውን የእግዚአብሄርን የፍቅር ስሜት መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ውስጥ የተለየ መፍሰስን ሊሰጥ ይችላል፡፡

5.የጳውሎስ 4ኛ ጥያቄ፡ በቁ 4 ላይ ጳውሎስ ያ መከራና በዚያን ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ድጋፍን መለማመድ ከንቱ ሊሆን እና ሊረሳ እንደሆነ ጳውሎስ ይጠይቃል?

ጥያቄ 5፡ በቁ 5 ላይ መንፈስ ቅዱስ ለነርሱ የተሰጠበት መሰረት ምን እንደነበረ ይጠይቃል፣ በህግ ስራ ወይስ በእምነት መስማት ነበር?

ጳውሎስ መልሱን በግልጽ ይጠብቃል፤ "በእምነት መስማት ነበር።"

ሀ) "እዚህ ላይ ጳውሎስ "የህግ ስራ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

(3፡10-14፤ 5፡2-4 እና 6፡13ን ተመልከት)

"በህግ ስራ" ሲል ጳውሎስ ህጉ ለሚያዘው ሁሉ ሙሉና ቀጣይ መታዘዝ ማለቱ ነው።

(በገላ 3፡10-14 ከዘዳ 27፡26 ላይ ይጠቅሳል። በዛዳ 27 ብዙ ጣኦት አምላኪዎች፣ ሞራል የሌላቸውና የአመጽ ስራዎች ተረግመዋል።)

ለ) "በእምነት መስማት" ሲል ምን ማለቱ ነው?

"የእምነት መታዘዝ" ሲል ጳውሎስ የጸጋውን ወንጌል መስማትና እሱን ለመስማት በተጨማሪም እርሱን ማመን እና እምነትን መለማመድ፣ ለእነርሱ በተሰበከው ክርስቶስ መታመን ማለት ነው።

ወንጌል ለእርሱ በተሰበከ ጊዜ አብርሃም ያደረገው ነገር ይህን ነበር (ቁ. 7-9)።

ከ2፡16 እስከ ምዕራፍ 3 የጳውሎስ ክርክር ፍሰት፡

1.በህግ ስራ ሳይሆን በተሰቀለው ክርስቶስ በማመን ጸድቀናል (2፡16እና 21ን ተመልከት)

2.ወንጌልን ስንሰማ እና በተሰቀለው ክርስቶስ ስናምን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንቀበላን (3፡1-2)

3.በእምነት ነው የእግዚአብሄርን ታምራዊ ሃይል በህይወታችን የምንለማመደው (3፡5)

በዚህ መንገድ ነው ሁልጊዜ ደህንነት የሚመጣው እና የሚለማመደው።

ለአብርሃም እንዲህ ነበር በትክክል የሆነው

1.በእምነት ነበር የጸደቀው 3፡6

2. እግዚአብሄር በደስታና እርሱን በማረጋገጥ ባርኮል፣ ሮሜ 4፡3-11

3. በእምነት ቀጥሏል እግዚአብሄርም በህይወቱ በታምራት ሰርታል ሮሜ 4፡18-21 እና ዕብ 11፡11-12

1ሐ. እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆች እነማን ናቸው?

6.በቁ 7፣ 8 እና 9 ውስጥ ተደጋገመው ቃል የትኛው ነው?

"እምነት" የሚለው ቃል ነው

7.የገላትያ ክርስቲያኖችን ሲያስቸግሩ የነበሩት "የአብርሀም ልጆች" ስለመሆን እየተመኩ ነበር። (ማቴ 3፡9 እና ዮሐ 8፡33ን ተመልከት)።

እውነተኛ የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ ጳውሎስ የሚናገራቸው እንማን ናቸው?

8. ከቁ 8 ወንጌል ተስፋ የሚሰጠው መሰረታዊ በረከት ምንድን ነው?

(መሠረታዊው እና ዋናው በረከት?)

የጽድቅ በረከት።

9.ከቁ 6 ይህ መሠረታዊ በረከት ምን ማት ነው?

የራሳችን ያልሆነ ጽድቅ አለን ማለት ነው ግን የእኛ እንደሆነ ተቆጠረልን ማለት ነው።

2.ህግና ወንጌል

2ሀ.ህግ ርግማንን ያመጣል። ወንጌል ብቻ በረከት ያመጣል

ጳውሎስ ስለ ዘላለም ህይወት ግድ ይለዋል።

እንዴት እንደምናገኘውና እንዴት እንደምንኖረው።

ጴጥሮስን አስብ! በአንጾኪያ መኖር እንደሚገባው የዘላለም ህይወትን እየኖረ አልነበረም (2፡14-16)

ገየላትያ ሰዎችም የክርስትና ህይወትን እንዳጀማመራቸው እየኖሩት አልነበሩም (3፡3)።

ይህ ከእውነት የመራቅ ጉዳይ ጳውሎስን በጣም ረብሾታል።

የክርስትና ህይወትን የማግኛና የመኖሪያ መንገድ እውነተኛ እና ብቸኛው መንገድ የወንጌል መንገድ ነው። በክርስቶስ **የማመን ፣ በመንፈስ ቅዱስ ህይል ነው የሚኖረው ።**

የክርስትና ህይወትን በህግ መንገድ ማግኘትና መኖር የማይቻል ነው።

ዘላለማዊ ህይወትን ለማግኘት ጽድቅ ያስፈልገናል።

የዘላለም ህይወትን መኖር በጽድቅ መኖር ነው።

10. በቁ 11 ጻድቅ እንዴት ነው የዘላለም ህይወት የሚያገኘው እና የሚኖረው?

"በእምነት" ነው የሚያገኙትና የሚኖሩት።

11. በቁ 12 በእምነት ሳይሆን በህግ መንገድ የሚከተሉት የዘላለም ህይወትን ለማግኘት ማድረግ የሚገባቸው ምንድን ነው?

ህጉን በሙሉ መታዘዝ አለባቸው (ለሀጢአተኛ ሰው ያ ግን የማይቻል እይደለም! ቁ 10)።

12. ሰውየው መስራት እና ህይወትን በእርሱ መምራት ካበት ህጉ የሚጠቀው መታዘዝ ምን አይነት መታዘዝ ነው? (ቁ 10) (ያቆብ 2፡10-11ንም ተመልከት)

ማንም ሰው በእርሱ ህይወትን ማግኘት ካለበት ህጉ ቀጣይ፣ የተሟላና እውነተኛ መታዘዝን ይፈልጋል።

አንድ ቦታ ላይ ህጉን መስበር ማለት ሁሉንም መስበር ማለት ነው ምክንያቱም ሁሉም እንደ አንድ የህይወት ህግ ስለሆኑ።

13 በቁ 10 ላይ ህጉን በመታዘዝ የዘላለም ህይወትን መኖርና ማግኘት እነደሚችሉ ስለሚያስቡት ሰዎች ጳውሎስ ምንድን ነው የሚናገረው?

በትክክል ከእግዚአብሄር እርግማን ስር እንዳሉ ነው የሚናገረው።

14.እነዲህ ያለ ነገር ለመናገር ጳውሎስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ አለውን?

(ቁ 10 እና 11)

አዎን፣ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ከዕንባቆም 2:4 የተወሰደ ጥቅስ ነው።

15. በህግ መንገድ እና በእምነት መንገድ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? **(ቁ 12)**

ሕጉ ህይወትን ለማግኘት ጽድቅን ራሳችን እንድንሰራው ይጠይቃል።

የእምነት መንገድ ህይወት ነጻ ስጦታ ሆኖ እንዲሰጠን የክርስቶስ ጽድቅ ላይ እንድንመሰረትና የክርስቶስ ጽደቅ እንዲሰጠን ይነግረናል።

16. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ "መርገም" ወይም "የተረገመ" የሚለውን ቃል አምስት ጊዜ ይደግመዋል።

"የተረገመ" ማለት ምን እንደሆነ እነዚህን መጽሀፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች አስብ፡ ይህንን ለማስረዳት ጥቂት ምሳሌዎችን መስጠት ትችላለህን?

እባቡ - ዘፍ 3:14-15

የተረገመ በመሆን፡

- *ወደ ምድር ተጣለ*
- *እግዚአብሄር ተቃወመው*
- *በጥፋት ተደመሰሰ*

ምድር - ዘፍ 3:17

- *ስቃይ ያመጣል*
- *ችግሮች (እሾህና አሜኬላ)*
- *እና ሞትን ያመጣል*

አመንዝራዋ ከተማ - ዘዳግ 13:12-16

- *ለሰይፍ ተሰጠች*
- *ለጥፋት ታልፋ ተሰጠች*
- *በሀይለኛ የእግዚአብሄር ቁጣ በእሳት ተቃጠለች*

አመጸኛዋ እስራኤል - *ዘዳግም 28፡ 15-68*

በእስራኤል ህዝብ ላይ ርግማንን የሚያጣ ዝርዝር በሙሉ እዚህ አለ

ኢያሪኮ - ኢያሱ 6፡17-18 እና 26

- *ለጥፋት ተሰጠች*
- *ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ሞት*

17.ከጥያቄ 16 መልሶች ፣ በተረገመ ጊዜ በመስቀል ላይ ስለተሰቃየው ስቃይ አስብ! (ቁ 13)

እዚህ ላይ የራስህን መልስ መስጠት አለብህ።

18.ወንጌልን በመስበክ ጊዜ ክርስቶስ ለእኛ የተረገመ እንደሆነ መቅረብ ያለበት እንዴት እንደሆነ አስብ (ቅጽ 1 ገጽ 20ን ተመልከት)

እዚህ ላይ የራስህን መልስ መስጠት አለበህ

19.ከቁ 14 እና ከቁ 8-9 በተሰቀለው ክርስቶስ አማካኝነት የተቀበልነው ሁለት በረከቶች ምን ምን ናቸው? ቁ 1-2ን ተመልከት

በክርስቶስ ስናምን የተቀበልናቸው፡

i. *ጽድቅ (ቁ 8፣9)*
ii. *ተስፋ የተገባውን መንፈስ ቅዱስን (ቁ 14 እና 1-2)*

2ለ. ህጉ በወንጌል ላይ ምንም አልተጨመረም ደግምም ምንም ለውጥ አላደረገም።

ጳውሎስ ከኪዳኖች እውነታዎች ጋር ያስተዋውቀናል።

እግዚአብሄር በታሪክ ውስጥ ብዙ ኪዳኖችን ገብቷል።

- *በኖህ አማኝነት ከመላው አለም ጋር - ዘፍ 6፡17-19፣ 8፡20-9፡17 (የቃል ኪዳን ምልክት= ቀስተ ደመና)*
- *ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር - ዘፍ 12፡1-3፣ 15፡1-21፣ 17፡1-27 (የኪዳን ምልክት = ግርዘት)*
- *በሲና ተራራ ከእስራኤል ጋር - ዘዳ 5*
- *ከዳዊት ጋር - 2 ሳሙ 7፡8 -17፣ 23፡5፣ መዝ 89፡33-37፣ ኢሳ 55፡3*
- *አዲስ ኪዳን - ኤር 31፡31-34 ዕብ 8፡8-12 እና 10፡16፣17፣ ሉቃስ 22፡19*

- *እነዚህ ሌሎቹ ኪዳኖች በእግዚአብሄር ልዩ ተስፋዎች አሏቸው፤ በአንዳንዶቹም በመሃላ ምሏል እርሱ ራሱ እንደሚጠብቃቸው።*

20.ቁ 15 ላይ ከሰው ኪዳኖች ምሳሌ በጳውሎስ የተላለፉት መልእክቶች ምን ምን ናቸው?

አንዴ ከተጠናቀቀ እና ከተፈጸመ በኋላ የሰው ኪዳን ሊጨመርበት፣ ሊሰረዝ ወይም የማሰይራ ሊሆን አይችልም።

21. የተስፋ ቃሎቹ የተገቡለትና ፍጻሜ የሚገኝበት ከአብርሃም ጋር የተደረገው ኪዳን ብቸኛ ወራሽ ማን ነው?

ተስፋ ቃሉ የተገባለትና የሚፈጸመበት የአብርሃም አንድ ዘር ክርስቶስ ነው (2 ቆሮ 1፡20ን ተመልከት)

22. የሰው ኪዳኖች የማይሰረዙ ወይም የማይቀየሩ እንደሆኑ በማሰብ (ቁ. 15)፣ በቁ 17 እና 18 ስለሙሴ ህግና ከአብረሃም ጋር በተገባው ኪዳን ላይ ባለው ተጽኖ ላይ ጳውሎስ ምን እያስተላለፈ ነው?

ህጉ የመጣው ከአብርሀም ጋር የተደረገው ኪዳን ከተፈጸመ (ከተረጋገጠ፣ ሳንክሽንድ፣ ኦቶራይዝድ) ከተደረገ ከረጅም ጊዜ በኋላ ስለሆነ፣ለፍጻሜው አዲስ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ህጉ ሊሻረው ወይም ሊቀይረው አይችልም።

23. ቁ 18 በተስፋ ቃል የመጣ ቃል የተገባ ነገር ምንድን ነው?

(ቁ 14 እና 4፡1-6)። (ሮሜ 4፡13፣8፡17፣ ዕብ 1፡2፣2፡3-5፣ እና ኤፌ 1፡11-14፣ ሮሜ 8፡20-23ንም ተመልከት)።

ተስፋ የተሰጠው ርስት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው።

ገላ 3፡14 "ተስፋ የተሰጠውን ተስፋ እንቀበል ዘንድ።"

ገላ 4፡1-6 ክርስቲያች "አባ አባት" ብለው እንዲጮሁ የእግዚአበሄር ልጅ መንፈስ ተሰጥቶአቸዋል።

ክርስቲየናኖች አለምን የሚወርሱ ናቸው። ሮሜ 4፡13 (ማቴ 5፡5)።

ከክርስቶ ጋር እርሱን አብረው የሚወርሱ ናቸው።። ሮሜ 4፡13 - ሮሜ 8፡17 እ ዕብ 1፡1-2 እና 2፡3-5 (የሚመጣው አለም፣ አዲስ ፍጥረት)።

ኤፌ 1፡11-14 ክርስቲያች እንደርስታቸው ክፍል እና ሙሉ ርስታቸውን እንደሚከተል ዋስትና በመንፈስ ቅዱስ ታትመዋል።

ሮሜ 8፡20-23 ክርስቶስ ሲመለስ እንደሚገኘው ሙሉ የደህንነት በኩር ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል።

24. ርስቱ በህግ እንዲሁም በተስፋ ቃል መሆን የማይችለው ለምንድን ነው?

ርስቱ በህግም በተስፋም መሆን አይችልም ምክንያቱም ሁለቱ የተለያዩ ሥርዓቶች ናቸው።

ህግ የሚሰራው በሰው ጥረት ነው የእግዚአብሄር የተስፋ ቃሎች ግን በእግዚአብሄር ጸጋ መሠረት ነው የሚሰሩት።

ህጉ የሚሰጠን የተገባንን ብቻ ነው ጸጋ ግን የማይገባንን ነገር ነው የሚሰጠን።

ህግ ለደህንነት በፍጹም ዋስትና አይሆንም። በርግጥ ህጉ ለቁጣ ነው ዋስተና የሚሰጠው፣ ሮሜ 4፡5።

የጸጋ ተስፋዎች ላመኑ ሁሉ ለደህንነት ዋስትና ይሰጣሉ። ተስፋ ለፍቅር ዋስትና ይሰጣል።

ገላ 3፡19-25

2ሐ. ህግ ለም ተሰጠ ለምንስ ተወሰደ;

ጳውሎስ እዚህጋ መልስ ይሰጣል፡ "ህጉ የተስፋ ቃሉን ካለወጠ ወይም ለርሱ ምንም ካልጨመረ ለምን ተሰጠ" ብሎ ይናገራል።

25.የህጉ መምጣት ለሀጢአት ምንድን ነው የሚሰራው?

- **ሮሜ 3፡19**

  ህጉ ሁሉንም በደል ይኮንናል ስለዚህ ሁሉንም ሰው በእግዚአብሄር ፊት ሀጠአተኛ ነህ ብሎ ዝም ያሰኛል።

- **ሮሜ 5፡20**

  ህጉ የተሰጠው ስንት ነገሮች ሀጢአተኛ እንደሆኑ ለማሳየት ነበር። ከሰዎች አስተሳሰብ በላይ የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ።

- **ሮሜ 6፡7-13**

  ህጉ የተሰጠው የሀጢአትን እውነተኛ ምንነት እና አስከፊነት ለማሳየት ነበር፤ እንዴት ሀይለኛና ሊቃወሙት የማይችሉት እንደሆነ ለማሳየት ነበር።

26. ህጉ ለምን ያህል ጊዜ ነበር እንዲሰራ የታቀደው? (ቁ 19)

እንደ ስርኣት ህጉ የተሰጠው በአብርሀም ተስፋ የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ ነበር። ክርስቶስ እስኪመጣ ጥቅም ላይ መዋል ነበረበት።

27. ስለ ህግ መሰጠት ጳውሎስ ሊያስምርበት የፈለገው ምንድን ነው; (ሐዋ ስራ 7፡53፣ ዕብ 2፡2 እና ዘዳ 5፡4-5፣ ዘጸ 20፡18-21፣ ዘዳ 5፡23-31ንም ተመልት)።

ህጉ ሲሰጥ መላእክቶች እንደነበሩ እና ከእግዚአብሄር ዘንድ በመካከለኛነት ለሰዎች እንደተሰጠ ጳውሎስ ግልጽ ያደርጋል።

መካከለኛ በሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል የሚቆም የሆነ አካል ነው።

በቁ 20 ጳውሎስ "እግዚአብሄር አንድ ነው" በማለት ይጽፋል።

እነዚህን ቃለት ለመግለጽ የሚሞክሩ በርካታ ትርጉሞች አሉ።

አንዱ ትርጉም፡

ህጉ በሚሰጥበት ጊዜ፣ በሁለት ቡድኖች መካከል ሚድዬሽን ነበር፣ ተስፋው በሚሰጥበት ጊዜ ግን እግዚአብሄር ብቻ ነበር የተሳተፈው።

በቀጥታ ነው የተሰጠው ስለዚህ እግዚአብሄር አንድ ነው" ማለት "ተስፋው በሚሰጥበት ጊዜ፣ እግዚአብሄር ብቻውን ነው ያደረገው" ማለት ነው።

ሌላኛው ትርጉም

መካከለኛ ማለት ከአንድ ፓርቲ በላይ ያሳያል፣ ከነዚህ ቡድኖች ውስጥ "እግዚአብሄር ግን አንድ ነው"!

ይህንን ትርጉም እመርጣለሁ ምክንያቱም ከቁ 21 ጥያቄ ጋር በተሻለ ሁኔታ ፍሰት አለው።

የቁ 21 ጥያቄ ከዚህ ከሁለተኛው ትረጉም ቀጥሎ ይመጣል። **ህጉን በመስጠት እግዘኢብር አንዱ ቡድን ስለሆነ፣ ህጉ በእግዚአብኄር ህግ ላይ ተቃራኒ መሆን ይችላልን? እንደዛ ከሆነ፣ እግዚአብሄር ከራሱ በተቃረነ ሁኔታ ሊሰራ ነው ማለት ነው - ይህ የማይሆን ነው!**

28-ተስፋው አንድን አላማ ያገለግላል ህጉ ደግሞ ሌላን፤ እርስ በርስ የሚቃረኑ አይደሉም፤ እንዲሁ የተለያዩ ነገሮችን የሚያደርጉ ናቸው።

ህጉ መስጠት የማይችለው ነገር ምንድን ነው? ለምን? (ቁ 21)

ህጉ በጽድቅ ለመኖር የሚያስፈልገውን ወይም ህይወትን የሚያሸልም ጽድቅንም መስጠት አልቻለም። ህጉ ሊያድነን አልቻለም።

29. ቅዱሳት መጻህፍት ስለ ሰውና ስለ ሀጢአት የሚያስተምሩን ምንድን ነው (ቁ 22) ?

ቅዱሳት መጻህፍት ሰዎች በተፈጥሮ የሀጢአት እስረኞች መሆናቸውን ነው የሚያስተምሩን።

30.የሀጢአት ነጻነት የተሰጠው ለምድን ነው ቁ 22?

ነጻነቱ የመጣው ለሚያምን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው።

31. በቁ 23 እ 24 ጳውሎስ እንደመጣ የሚናገረው ምንድን ነው?

ሀ) እምነት መጣ፣ ቁ 23

ለ) ክርስቶስ መጣ፣ ቁ 24

32. በቁ 23 እና 24 ጳውሎስ እንደሚናገረው ህግ የነበረው ሁለት ሚናዎች ምን ምን ናቸው?

ሀ) አሳሪ፣ ምርኮኛ እና እስረኛ አድርጎ የሚይዘን። ቁ 23

ለ) ሞግዚት፣ ውሎአችንን ይቆጣጠራል ቁ 24

33.በቁ 25 እና 26 ክርስቶስ እና እምነት ሲመጡ፣ በአማኝ ህይወት ህጉ የነበረው ሚና ምን ሆነ?

34.በክርስቶስ እያንዳንዱ አማኝ ያለው አዲስ ማንነት ምንድን ነው?

ሁሉም አማኞች በክርስቶስ አሁን የእግዚአብሄር ልጆች ናቸው።

3.በክርስቶስ ሁሉም አንድ

3 ሀ. ለሁሉም ክርስቲያኖች እውነት የሆኑ አራት ነገሮች

ጳውሎስ "በክርስቶስ" የሚለውን ስያሜ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ሁሉ ይጠቀማል። እዚህጋ ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር በተገናኘ አራት እውነታዎችን ይጠቁማል።

1) **ወደ ክርስቶስ ተጠምቀዋል፡**

"ወደ ክርስቶስ መጠመቅ" (ቁ 27) ሲጀመር ስለውሀ ጥምቀት አይናገርም፣ (ምንም እንኳን ያ አስፈላጊ ቢሆንም)።

በህያው እምነት አንድን ሰው ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የማገናኘት የመንፈስ ቅዱስን ስራ ያመለክታል።

1 ቆሮ 12፡12-13ን ተመልከት

በ1 ቆሮ 12፡12-13 ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ስለተጠመቀ ክርስቶስ ስለሚያደርገው እየተናገረ አይደለም። (ማቴ 3፡11)።

መንፈስ ቅዱስ ስለሚያደርገው ወደ ክርስቶስ ስለመጠመቅ እየተናገረ ነው። (በአንድ መንፈስ)።

በመንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ እምነት መግባት ነው።

2) **"ክርስቶስን መልበስ" (ቁ 27) የአዲስ ማንነት መኖር ነው።**

አዲስ ማንነት ከሀጢአት እና ከእግዚአብሄር ጋር በተገናኘ፡

- ለሀጢአት ከዚህ በኋላ ባሪያ አለመሆን
- ከሀጢአት ፍርድ በታች አለመሆን
- ይቅር መባል እና ነጻ፣ የእግዚአብር ልጅ መሆን(ቁ 26)

3) በክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉም አንድ (ቁ 28) "ክርስቶን መልበስ"

በመንፈስ ቅዱስ ወደ እርሱ መጠመቅ ፣ የክርስቲያን በውሀ መጠመቅ ሲመላከት፣ ከየትኛውም ከሌላ ክርስቲያን ጋር በተያያዘ አዲስ ማንነት አለን፡፡

ሀ. የብሄር፣ የዘር ወይም የነገድ ልዩነት የለም

ለ. ማህብራዊ ገደቦች የሉም

ሐ. የጾታ ገደብ የለም

እኛ ሁላችንም "በክርስቶስ ኢየሱስ" አንድ ነን፡፡

በዮሐ 17፡20-23 የኢየሱስን ጸሎት ክፍል አንብብ፡፡

4) ከክርስቶስ ጋር አብሮ መውረስ፡ (29)

ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን ክርስቲያን ለአብርሀም የተሰጠውን የተስፋ ቃል ትክክለኛ ወራሽ ነው፡፡

(የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ ቁ 14)፡፡ በሚመጣው አለም ከክርስቶስ ጋር ወራሾች፤ ዕብ 2፡1-2 እና 2፡3–10፣ ማቴ 5፡5 እና ሮሜ 8፡16-17፡፡

ገላትያ 4

የምዕራፍ 4 ቅደም ተከተል	
1 በወራሾች ህይወት ያሉ ደረጃዎች	ሀ) የጨቅላ አመታት 1-3
	ለ) በእግዚአብሄር የተቀጠረ ጊዜ ፡፡ ተስፋ የተሰጠውን ተስፋ የሚያረጋግጥ የክርስቶስ ስራ ቁ 4-5
	ሐ) የተሰጠ ርስትና ለወራሾች አዲስ ማንነት ይህ ምን ማለት እንደሆነ ቁ 6-7
2 የገላትያ ሰዎች ሲያድረጉ የነበር አሳዘኝ ነገር	ሀ) ክርስቲያን ከመሆናቸው በፊት፣ ወደ ኃላ መመለስ!!!! የጳውሎስ አስቸኳይ ልመና ፡፡ እርሱን ምሰሉ ቁ 8-12
	ለ) ጳውሎስን የመምሰል የአመለካከት ለውጥ ቁ 13-16
	ሐ) ሌሎችን በእስራት ውስጥ አድርጎ የሐሰት አስተማሪዎቹ ምስጋና ማግኘት፡፡ የጳውሎስ አስተምህሮና ምጥ በክርስቶስ መላትንና ነጻነትን ለመስጠት ቁ 17-20
3 ሁለቱ ኪዳኖች	ሀ) የአብርሃም አካላዊ ልጆች እውነተኛ ታሪክ ቁ 21-23
	ለ) የአብርሀም ስጋዊ ልጆች መንፈሳዊ

በወራሾች ህይወት ውስጥ ያሉ ደረጃዎች

1 ሀ) ቁ 1-3 የጨቅላነት አመታት

በገላ 3፡23-25 ከእምነትና ክክርስቶስ መምጣት በፊት ጳውሎስ ስለ ህይወት ተናግሯል።

ህጉ እንደ "ሞግዚት" የሰራበት ጊዜ ነበር። ስዕሉ ከእድሜ በታች ያለ ልጅ ነው፣ አባቱ ለሞግዚት ከባሪያ በታች የተወው። የሞግዚቱ ስራ ልጁ ትምህርተ ቤት መግባቱን እና ዘወትር በአግባብ መመላለሱን ማረጋገጥ ነው። ህጉ ያ ነው ስራው፣ ትምህርቱን ማረጋገጥ እና ከበታቹ ያሉትን ሰዎች ባህሪ መምራት።

በገላ 4 ጳውሎስ ምሳሌውን ያስፋፋዋል፣ ልጁ ዕድው እጨመረ ሲሄድ የልጁን ዕድገት በመከተል።

1.በዚህ ጊዜ ወራሹ በህይወቱ ከባሪያ የማይለየው ለምድን ነው?

ወራሹ ገና ልጅ ነው ደግሞም እንዴት እንደሚርኖር ገና እየተማረ እና እሰለጠነ ነው።

2.የዚህ ወራሽ ይህ ደረጃ አስከመቼ ነው የሚቆየው?

አባቱ እስከወሰነው ጊዜ ወራሹ እንደ ልጅ ይታያል። ተስፋ የተሰጠውን ውርስ ልጁ ለመውረስ አባቱ ሁሉም ነገር ዝግጁ መሆኑን ሲያስብ።

1 ለ) ቀ. 4-5 በእግዚአብር የተቀጠረ ሰዐት

3 በልጁ/ በወራሹ መንፈሳዊ ተዛምዶ ምሳሌ ውስጥ፡

ሀ. ህጻን የሆኑት ልጆች እነማን ናቸው?

በዚያን ጊዜ የነበሩ ሁሉም ክርስቲያኖች በወራሹ ህጻን ተመላክተዋል፣ ጳውሎስ እና የገላትያ ክርስቲያኖች ቁ 3

ለ. "እንደ ሞግዚትና ተቆጣጣሪዎች" የሚሰራው ማን ነው?

i. ጳውሎስ እንደ አይሁድነቱ፣ ህጉ እንደሞግዚቱ ሆኖ አገልግሏል 3፡24፣ (4፡5 "ከህግ በታች" እና ቁ 21)።

ii. ለገላትያ ሰዎች አይሁድ እንዳለመሆናቸው፣ (አህዛብ) "የአለም መሰረታዊ መርሆች" እንደሞግዚታቸው አገልግሎአል 4፡3

ሁለቱም በእግዚአብሄር የተሰጡ መሠረታዊ ህጎች ነበሩ አንዱ በልዩ መገለጥ እና በማዳኑ ጸጋ የተሰጠ፣ ሌላው ደግሞ በተፈጥሮ መገለጥ እና በተለምዶ ከልካይ ጸጋ።

ሐ. ከእድሜ በታች ያለው የዚህ ባሪያ ደረጃ የሚያልቀው መቼ ነው?

የእግዚአብሄር አብ የተወሰነው ጊዜ ሲመጣ ያበቃል። ወደ አለም ልጁን ለመላክ ጊዜው በደረሰ እና ታላቁን የደህንነት ስራ ሲሰራ።

4.በቁ 4 እና 5 ውስጥ በእግዚአብሄር አብ የተቀጠረውን ጊዜ ከህጉ ሞግዚትነትና አደራ በታች ልጆቹን አውጥቶ ወደ ልጆች እና ወራሾች ነጻነት ለማምጣት የሚያሳዩ አራት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

i. እግዚአብሄር ከሰማይ ልጁን ልኳል

ii. ልጁ እንደ ሰው ተልኳል። በማርያም ተጸንሶ ተወልዷል ገና ድንግል ሳለች።

iii. ከአይሁድ ህዝብ ስለዚህም ከእግዚአብሄር ህግ በታች ተወልዷል

iv. የእርሱ ስራ ከህጉ መስፈርት ለህዝቡ ነጻነት መክፈልና ከህጉ እነርሱን ነጻ ማውጣት ነበር። እነርሱን መዋጀት።

1 ሐ) የተሰጠው ውርስ

5.ጳውሎስ ክርስቲያኖች እንደተቀበሉት የሚናገረው በረከትና ርስት ምንድን ነው? (ቁ 5 እና 6)። (3፡2፣5፣9፣14፣18 እና 29ንም ተመልከት)።

የተሰጠው በረከት እንደ ልጆች መሆን ነው (ለውርስ የደረሱ የልጆች ደረጃ)።

የተቀበልነው ርስት የእግዚአብሄር ልጅ መንፈስ ወደ ልባችን መላኩ ነው።

6.ተስፋ ስለተሠጠው መንፈስ ቅዱስ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚነግሩን ምንድን ነው?

- ዮሐ 4፡13-14ን ከ ዮሐ 7፡37-39
- ዮሐ 14፡15-18
- ሐዋ 1፡4 እና 5
- ሐዋ ስ 2፡38
- ሐዋ 10፡44-48
- ሐዋ 19፡2
- ሮሜ 5፡5

7.የወልድ መንፈስ የተሠጠው ለማን ነው? (ቁ 6 ገላ 3፡26ንም ተመልከት)

የወልድ መንፈስ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የእግዚአብሄር ልጆች ለሆኑት ሁሉ አሁን ተሰጧል።።

እዚህጋ በጣም ጥቂት አስፈላጊ የሚያዙ ነጥቦች አሉ፡-

***ሀ*) እንደ ልጅነት መንፈስ መንፈስ ቅዱስን መቀበል በዳግም መወለድ የመንፈስ ቅዱስ ስራን ከመቀበል የተለየ ነው።።**

ነገር ግን

ለ) እያንዳንዱ የተለወጠ (ዳግም የተወለደ ሰው) በዚህ በክርስቲያ ዘመን (በክርስቶስ እርገት እና መምጣት መካከል ያለው ዘመን)መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል፣ ተስፋ ከተገባላቸው ርስት ሳይሰጣቸው እግዚአብሔር አይተዋቸውም።።

ዳግም መወለድ በእኛ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው።።

ልጅነት ለእኛ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው።።

ፕሮፌሰር ጆን ሙሬ እንዲህ ጽፏል፡

“የማደጎ ስራ በአዲስ ኪዳን ግልጽ ባለ ሁኔታ መታየቱን እውነታ ማድነቅ አለብን፤ ልጅነት ከዳግም መወለድ ፍጹም የተለየ እንደሆነ ግልጽ ነው።። . . . ልጅነት በዳግም መወለድ እንዲሁና እና ብቻ እንደተቋቋመ ማሰብ ካለብን ስማደጎ አስፈላጊነት ፣ እውነታ እና ልዩ ጸጋ በተሳሳተ መንገድ እየተረዳን ነው ማለት ነው።።”

ኮሌክትድ ራይቲንግስ ቅጽ 2 ገጽ 227፣ በ1984 ድጋሚ በታተመው፣ ባነር አፍ ትሩዝ

8.ተስፋ የተገባው “የማደጎ መንፈስ” ዳግም ለተወለዱ ለእግዚአብሄር ልጆች የተሰጠው ክርስቶስ ከመክበሩ በፊት ነውን? (ቁ 15)

መልሱ አይደለም መሆን አለበት። ይህ የብይ ኪዳን አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ስራን አልተለማመዱም ማለት አይደለም፣ ተለማምደዋል፣ ነገር ግን ይህ የተወሰነ ተስፋ የተገባ በረከት የክርስቶስን የተፈጸመ ስራ እና የእርሱን መክበር የጠበቀ ነበር። ዮሐ 7፡ 37-39ን ተመልከት።

9.ከታች ያሉት ጥቅሶች መንፈስ ቅዱስን እንዴት ነው የሚገልጹት?

- 2 ቆሮ 1፡21-22
- 2 ቆሮ 5፡5
- ኤፌ 1፡13 እና 14

10. "ማህተም" እና "የርስታችን መያዣ" ምን ማለት ናቸው?

ማህተም የባቤትነት ዘፍ 38፡17-18 እና 25፣ 2ጢሞ 2፡19 እና የጥበቃ ምልክት ነው ዳን 6፡17፣ ማቴ 27፡65-66፣ ራእይ 5፡1።

የመንፈስ ቅዱስ ማህተም አማኞች ለነርሱ ትልቅ መጽናናት የሆነው የእግዚአብሄር የራሱ የተለዩ ልጆች መሆናቸውን ያሳያል፤ ለዘላለም የተጠበቁ መሆናቸውንም ያሳያል። (1ዮሐ 4፡4 እና ሮሜ 8፡11ን ተመልከት)

ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ "መያዣ" ነው ሲል "አስተማማኝ" ሙሉ ተስፋው በኋላ እንደሚሰጥ የሚረጋግጥ በቅድሚያ የሚሰጥ ቀብድ ማለት የሆነውን አራቦን የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀማል።

መንፈስ ቅዱስና እርሱ የሚሰጠው ሰላም፣ ፍቅርና ቅድስና አማኞች በስተመጨረሻ የሚደሰቱባቸው የሰማይ ሰላም፣ ንጽህና እና ፍቅር ምሳሌ ናቸው።

11.እግዚአብሄር የልጁን መንፈስ ወደ አማኞች ልብ የመላኩ ውጤት ምንድን ነው?

(ቁ 6) ሮሜ 5ን ፣ 8፡15ን፣ 17ን ፤ ዕብ 8፡7፡13 በተለይም ቁ 11ን ከሐ 17፡3 ጋር ተመልከት።

አማኞች መንፈስ ቅዱስ ውስጣቸው በመኖሩ አባታቸው እንደሆነ በእውነተኛ መንፈስ ወደ እግዚአብሄር መጮህ ይችላሉ።

ፍቅሩን ያውቃሉ፣ የእርሱ ልጆች መሆናቸውን ይረዳሉ፣ እርሱንና ይቅርታውን ይገነዘባሉ። እግዚአብሄርንና ጌታ ኢየሱስን ማወቅ አዲስና ዘላለማዊ ህይወታቸው ይሆናል።

ፕሮፌሰር ጆን ሙሬ በድጋሚ፡

"**መዋጀት** - ልጅነት የበረከት ሁሉ ቁንጮ እንደሆነ ያንጸባርቃል ደግሞም ያረጋግጣል።

መጠራት ወደ ልጁ ህብረት ይጠራናል

ዳግም መወለድ ያንን የመመሳሰል መርህ በጽድቅና በቅድስና ለእግዚአብሔር አምሳል ያመጣል።

መጽደቅ - ጻድቅ እንደሆነ በእግዚአብሄር ፊት ተቀባይነትን ይሰጣል፤ የተቆጠረው ጽድቅ የሚጠይቀውንም መስፈርት ለዘላለም ህይወት ስምን ይሰጣል።

መቀደስ ለእግዚአብሄር ህዝብ ልጅነት የተገባውን የእግዚአብሄር ወራሽነትን ሙሉ እና የርስት የመጨረሻ ደስታን ያዘጋጃል።

ነገር ግን በማደጎ ስራ ነው መለኮታዊ አባትነት ለፍጥረት የተገባ ነው በሚል ከፍ ባ ትርጉሙ እግዚአብር ለተዋጁት አባት የሆነው።" (ልክ አንደ ላይኛው፣ ገጽ 228)

12. በ4፡7 ላይ ጳውሎስ የሚያሰምርበት ነገር ምንድን ነው?

ንጽጽሩ ክርስቶስና እምነት ከመምጣቱ በፊትና በኋላ በነበረው በእግዚአብሔር ልጆች ምንነት መካከል የተደረገ ነው።

በፊት	በኋላ
ርስታቸውን በተመለከተ ልጆች ከባሪያ የተለዩ አልበሩም ቁ 1።	ልጆች በርስታቸው መደሰት የጀመሩ ልጆች ሆነዋል።

2.የገላትያ ሰዎች እያደረጉት የነበረ አሳዛኝ ነገር

2ሀ. እርሱን እንዲመስሉ የጳውሎስ አስቸኳይ ልመና ቁ 8-12

13.በቁ 8 እና 9 ጳውሎስ ሊረዳው ያልቻለው ነገር ምንድን ነው?

የገላትያ ሰዎች የመጨረሻውን የምስራች ሃይልና ጥቅም ከተለማመዱ በኋላ ወደ ሀይል አልባ፣ ጥቅም አልባ፣ ተራ ነገር ለምን እንደተመለሱ ጳውሎስ መረዳት አይችልም።

ልጅነትን እና ወራሽነትን ለባርነት ለምን እንደለወጡ መረዳት አይችልም!

14.ጳውሎስ የአህዛብ አማኞችን የመሰለው በምን መንገድ ነው? (ቁ 12); (ገላ 2፡14ንም ተመልከት)።

ጴጥሮስ እንደሆነው ሁሉ በውልደት ጳውሎስም አይሁድ ነበር፤ እንደ አንድ አይሁድ በህግ ነበር ያደገው ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አማካኝነት ልክ እንደ ገላትያ አህዛብ፣ ከህግ በታች አልነበረም።

15. የገላትያ ሰዎች ጳውሎስን ያልመሰሉት በምን መንገድ ነው? (ቁ 9 እና 10)

የገላትያ ሰዎች ከእግዚአብሄር ጋር ባለ ግንኙነታቸው ራሳቸውን ከህግ በታች ማድረጋቸው ነበር ጳውሎስን ያልመሰሉበት መንገድ

2 ለ. ጳውሎስን የመምሰል አመለካከት ቁ 13-16

ጳውስ ወንጌልን ወደ እነርሱ ባመጣ ጊዜ የገላትያ ሰዎች እንዴት ተቀብለውት እንደነበር ጳውሎስ መጻፍ ይጀምራል

- **አላሳዘኑትም ነበር**
- **አልናቁትም፣ አላፌዙበትም ነበር**
- **እርሱ ራሱ ክርስቶስ እንደሆነ አድርገው ነበር የተቀበሉት**
- **አይናቸውን እንኳን በመስጠት ችግሩን እስከማቃለል ቢረዱት ነበር የደስታቸው ብዛት የነበረው**

ነገር ግን ከጳውሎስ ጋር የነበረው ግንኙነታቸው በውጫዊ ሰዎች ተመረዘ።

በቁ 17 ውስጥ ጳውሎስ "እነርሱ" ብሎ ይጠራቸዋል። አላማቸው ክፉ ነበር። ከክርስቶስ የደህንነት መንገድ እነርሱን ለማውጣት እና ለራሳቸው ተከታይ ለማፍራት በጳውሎስና በገላትያ ሰዎች መካከል ችግር ማስቀመጥ ፈለጉ። ምናልባት እነዚህ ተቃዋሚዎች የገላትያ ሰዎች ጳውሎስን በመልካም መቀበላቸው ስህተት እንደነበር ነግረዋቸው ይሆናል። የእነርሱ አቀባበል ግሩም ከሆነ ህግን ከመከተል የአይሁድን አኗኗር በመተው እንዲኖር እንዳበረታታው።

ጳውሎስ "ምንም አልበደላቸሁኝም!" በማለት አጥብቆ ይናገራል። የሰበከው መልእክት ህግን የመተው ስህተት አልነበረም። የኢየሱስ ክርስቶስ መልእክት ነበር እነርሱም ያንን ያውቁ ነበር።

16. የጳውሎስን መልእክት ሲቀበሉ እንደዛ ያለ ደስታ የሰጣቸው በረከት ምን ነበር? ምዕ 3፡1-9

የመጽደቅና መንፈስ ቅዱስን እንደ ደህንነታቸው ማህተምና መያዣ መቀባላቸው።

(ማስታወሻ፡ በመጋቢ ላይ የጉባኤ መገልበጥ በእርሱ ላይ ምንም ነገር ከማምጣት ይልቅ የእነርሱ ለወንጌል እውነት ልል መሆንን ነው የሚያሳው።)

2ሐ. የሐሰት አስተማሪዎች ከጳውሎስ ጋር ሲነጻጸሩ ቁ 17-20

ጳውሎስ እንዴት እንደሚደግም ልብ በል፡ "በብርቱ ይፈልጉአችኋል" በቁ 17 ሁለት ጊዜ በቁ 18 አንድ ጊዜ

የመጀመሪያው "በብርቱ መፈለግ" ቁ 17 ውስጥ የሐሰት አስተማሪዎች በገላትያ ሰዎች ላይ የፈለጉትን ነገር ያሳይል። እንዴት እንደደለሉአቸው።

ሁለተኛው "ብርቱ መፈለግ" ቁ 17 ውሰጥ፣ የገላትያ ሰዎችን ያታለሉበትን መንገድ ያመለክታል።

የገላትያ ሰዎች “እነርሱን በብርቱ እንዲፈልጉአቸው” ነበረ፣ እንዲያከብሩአቸው፣ ከማንም ሌላ ሰው ይልቅ ከፍ አድርገው እንዲናገሩላቸውና እንዲያስቡአቸው።

ሶሥተኛው “በብርቱ መፈልግ” ቁ 18 ውስጥ ያለው፣ “በብርቱ መፈለግ” ለገላትያ ሰዎች የጳውሎስን አቀራረብ ያመልክታል፣ ከእነርሱ ጋር ሲሆን ብቻ አይደለም። አላማው መልካም ሲሆን ልዩ በሆነ እንክብካቤ መደረጉ መልካም እንደሆነ ያሳያል።

17. ከእነርሱ ጋር ሲሆን ብቻ ሳይሆን አሁንም ሲጽፍላቸው የገላትያን ሰዎች በብርቱ ሲፈልግ የጳውሎስ በጎ አላማ ምን ነበር?

በርግጥ ጳውሎስ የገላትያ ሰዎችን በብርቱ ፈልጓል። እነርሱ ለእርሱ የከበሩ ልጆቹ ነበሩ። ልክ እናት ልጆቿዋን እንደምትወድ ነበር የወደዳቸውና ያሳደጋቸው። ለእነርሱ የመሰጠቱ እና “እነርሱን በብርቱ የመፈለጉ” አላማ ክርስቶስ በእነርሱ እንዲሳል ነበር። የእግዚአብሄር ልጆች በልጁ መንፈስ ሲሞሉ ይበልጥ ክርስቶስን በመምሰል ያድጋሉ።

የአንድ እናት መሰጠት አብሮት መከራና ጭንቀት አለው። የጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች መሰጠት በእነርሱ መጠቃት ላይ ያምጣል ማለት ነው።

መጋቢ ወይም ወንጌላዊ ከሆንክ ለምንድን ነው ጉጉትህ?

“ህዝብህን በብርቱ ትፈልጋለህን?”

3.ሁለቱ ኪዳኖች ገላት ያ 4፡21-31

ትምህርቱን ለመግለጽ ጳውሎስ ቅዱሳት መጻህፍትን ይጠቀማል። የደህንነት ትምህርት ከቅዱት ጻህፍት ካልወጣ ተቀባይት ሊኖረው አይገባም።

ቁ 21 ላይ ያለው “ህጉ” የሚለው ቃል የሙሴ አምስቱን መጻህፍት ያመለክታል። ሰዎች በሙሴ ህግ ስር መኖር ከፈለጉ መላውን አስተምህሮቱን መስማት እንዳለባቸው ጳውሎስ ይናገራል። ዘፍጥረትን እና የአብርሃምን ቤተሰብ ዝዝር ጽሁፍ ስማ። የአብርሀም ቤተሰብ ታሪክ ወንጌልን ለመረዳት አስፈላጊ ነው። አብርሃም የአማኞች ሁሉ አባት ነው። የሲና ቃል ኪዳንንን፣ የህጉን ሚናም ያስረዳል። የአብርሃም ቤተሰብ ታሪክ አስፈላጊነት በዘፍ “16 እና 21 ውስጥ ሊነበብ ይችላል።

3ሀ. የአብርሀም የስጋ ልጆች እውነተኛ ታሪክ ቁ 21-23

18 በቁ 22-23 ውስጥ በሁለቱ ልጆች መካከል ጳውሎስ የሚገልጻቸው ሁለት ንጽጽሮች ምን ምን ናቸው?

1.*በእናቶቻቸው ስላለ ልዩነት።* አንዲቱ እናት ባሪያ ሴት ሌላኛዋ እናት ደግሞ ነጻ ሴት ነበረች።

2.*ስለተወለዱበት መንገድ፡፡* አንዱ ልጅ እንደ ስጋ ፈቃድ የተወለደ ነበር፡፡ ሌላው ልጅ ደግሞ ለተስፋው በሆነ ምላሽና መታመን ነበር የተወለደው፡፡

አብርሃም ወንድ ልጅ ተስፋ ተገብቶለት ነበር ከአመታት መጠበቅ በኋላ ግን ልጅ ለማግኘት ራሳቸው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ሳራ ሃሳብ አቀረበች (ዘፍ 16፡1-4)፡፡ አብርሃም የሳራ ገረድ ትሰጠዋለች፣ ለሳራ ትጸንሳለች ፣ ሳራ ልጁን ታሳድጋለች ፡፡ አብርሀም በእቅዱ ተስማማ አጋርም እስማኤልን ወለደችለት፡፡ ይህ ተስፋውን እንደሚጠብቅ በእግዚአብሄር ላይ ያልታመነ የሰው ስጋዊ ፈቃድ ነበር፡፡

በርግጥ እግዚአብሔር ኪዳኑን አላጠፈም ደግሞም በአብርሃምና በሳራ የመፍትሄ መንገድ አልነበረም የሚሰራው፡፡

ምንም እንኳን መካንና በእድሜዋም የገፋች ብትሆንም ሳራ ወንድ ልጅን እንደምትወልድለት ለአብርሃም አረጋገጠለት (ዘፍ 17፡15-19 እና 18፡9-15)፡፡

ጥንዶቹ የእግዚአብርን ተስፋ አመኑ ሳራም ለአብርሀም ልጅን፣ ይስሀቅን ወለደችለት (ዘፍ 21፡1-7)፡፡

19 ጳውሎስ "እንደ ስጋ ፈቃድ" ሲል ምን ማለቱ ነው ቁ 23?

"በስጋ" ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ይስሀቅም ልክ እንደ እስማኤል በተጸነሰበትና በተወለደበት መንገድ ነው በስጋ የተጸነሰውና የተወለደው፡፡

"ስጋ" ሲል ጳውሎስ "በወደቀው የሰው ጥበብና ጥረት" ማለቱ ነው፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብለህ 3፡3ን እና 5፡16-24ን ተመልከት፡፡ ፊሊ. 3፡2-7ንም ተመልከት፡፡

3ለ. የአብርሀም አካላዊ ልጆች መንፈሳዊ ትርጉም ቁ 24-27፡፡

20. ቁ 24 ላይ ሁለቱ ሴቶች ምን እንደሚወክሉ ነው ጳውሎስ የሚናገረው?

ሁለቱ ሴቶች ሁለቱን ኪዳን እንደሚያሳዩ ጳውሎስ ይናገራል፡፡

21. ቁ 24-25 ላይ አጋር የምትወክለው የትኛውን ኪዳን ነው?

አጋር የምታመለክተው እግዚአብሄር በሲና ተራራ ላይ ከእስራኤል ጋር የገባውን ኪዳን ነው፡፡

22. ከቁ 24-25 አጋር ስለምታመለክተው ኪዳን ጳውሎስ የሚናገረው ምንድን ነው?

በመጀመሪያ ባሪያ የሆኑ ልጆችን የወለደ ኪዳን እንደሆነ ይናገራል፣ ቁ 24፡፡ በመቀጠልም በኢየሩሳሌም ይደረግ የነበረው ባሪያ የሚያደርገውን ሀይማኖት እንደሆነ አጋር የምታመለክተው ይናገራል፡፡

23. ቁ 26 -27 ላይ በአንድ ወቅተ ላይ መካን የነበረችውን ሣራን ከየትኛይቱ ከተማ ጋር ነው የሚያነጻትራት?

ጳውሎስ ሣራን ከሰማይቱ ኢየሩሳሌም ጋር ያነጻፅራታል። ነጻይቱ ሴት ነበረች በርጅናዋም ጊዜ የይስሃቅ እናት በሆነች ጊዜ በደስታ ሳቀች።

24. የሲናን ኪዳን በሚከተሉትና ሣራን የሚወክለውን ኪዳን በሚከተሉት መካከል ያለው ንጽጽር ምንድን ነው? ቁ 24-28

1. ባርነት ከነጻነት ጋር

2. ትንሽ ደስታ ከትልቅ ደስታ ጋር

3. ጥቂት ልጆች ከብዙ ልጆች ጋር

4. ባርነት ከተስፋ ቃል ጋር

ይነጻፀራል።

25. ክርስቲያኖች ይስሀቅን እንጂ እስማኤልን የማይመስሉት ለምንድን ነው? ቁ 28

ክርስቲያኖች ይስሀቅን ይመስላሉ ምክንያቱም ውልደቱ ታምራዊና በእግዚአብሄር የተስፋ ቃል ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ነው (ዘፍ 15፡1-6፣ 18፡9-1 ሮሜ 4፡13-22 እና ዕብ 11፡11-12)።

በተመሳሳይ መንገድ እያንዳንዱ ክርስቲያን በተአምር ከላይ ተወለደ ይህ አዲስ ልደትም ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ላይ የተመሠረተ ነው (ዮሐ 3፡3-18 እና ገላ 3፡26)።

26. ቁ 29ን ተመልከት እና ይህን ጥያቄ መልስ፡ "ጳውሎስ በክርስቶስ ከመለወጡ በፊት ምን ነበር?" (ገላ 1፡23፣ ሐዋ 9፡1-2፣ 26፡4-12)።

የሀጉ አክራሪ ተከታይ እና ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ ነበር።

27. ሀጉን የሚከተሉ ሰዎች ኢየሱስን እና ክርስቲያኖችን የሚጠሉት ለምንድን ነው?

ሀጉ የደህንት እና የህይወት መንገድ ነው ብለው የሚከተሉ ሰዎች በስጋዊ ጥረት ደህንነትን እንደሚያገኙና እግዚአብሄርን ደስ በሚያሰኝ ህይወት እንዳልኖሩ ያምናሉ።

ክርስቲያናዊ መልእክት ደህንነትን በስራ ማግኘት እንደማይቻል ይናገራል። ደህንነት በጸጋ ነው በትጋት አይደለም፤ በእምነት አንጂ በስራ አይደለም፤ ሙሉ በሙሉም በሰው ጥረት ላይ ሳይሆን በእግዚአብሄ ስራ ላይ የተመሠረተ ነው።

በራሳቸው ጥረት የሚመኩ ሰዎች ወንጌል ዝቅተኛ፣ ደካማ እና አጸያፊ ይሆንባቸዋል።

ደህንነትን ለማግኘት በእግዚአብሄር የተስፋ ቃሎች ላይ የተመሰረቱትን ሰዎች በማሳደድ ምላሽ ይሰጣሉ።

ከቃየል ጊዜ ጀምሮ "ስጋዊ" ሰዎች የመንፈስ የሆኑትን አስገድለዋል።

28. ቁ 38 ላይ አጋርና እስማኤል ምን ሆኑ?

ከአብርሀም ቤት ተባረሩ። (ዘፍ 21፡8-20ን ተመልከት)። ይህ ማለት አጋርና እስማኤል መዳን አይችሉም ማለት ሳይሆን የስጋዊ መንገድን በመፈጸም መዳን አይችሉም ማለት ነው።

እንደ ሌላው የሰው ዘር ሁሉ በአብረሃም እና በተስፋው ዘር አማካኝነት ይባረካሉ ነገር ግን የስጋው እና የተስፋ ቃሉ መንገድ ሊቀላቀሉ አይችሉም።

29 ቁ 30 ላይ የአጋርና የእስማኤል መባረር ምን ያስተምረናል?

በሲና የተደረገው አሮጌ ኪዳንና በጌታ ኢየሱስ ደም የተረጋገጠው ስዲ ኪዳን ህብረት ሊኖራቸው እንደማይችል ያስተምረናል።

ከአጋርና ከእስማኤል ጋር መለያየት ለአብርሀም ጭንቅ እንደነበረው ሁሉ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያንም ከምድራዊቱ ኢየሩሳሌም እና ከምትወክለው ነገር መለየት ለብዙዎቹ በጣም ከባድ ነበር። ነገር ግን ልክ እግዚአብሄር የሳራን ቃል እንደሰማ ለአብርሃም እንደነገረው መለየት መኖር ነበረበት (ዘፍ 21፡11-12)።

ብዙ ክርስቲያኖችም አሮጌውና አዲሱ ኪዳን እንዴት እንደሚገናኙ ለማወቅ ይቸገራሉ።

ገላ 3፡21ን አስታውስና ስለ አጋርና ስለ ሳራ ግንኙነት የበለጠ አስብ።

የአጋርና የሳራ ግንኙነት፡

1. **ሁለቱም የአብረሀም ቤትሰብ ነበሩ**

ብሉይና አዲስ ኪዳን በአብርሀም ቤተሰብ ውስጥ ተመላክተዋል

2.በእነርሱ መካከል አስቸጋሪ ውጥረት ነበር፤ ልክ የሁለቱ ኪዳኖች ተከታዮች መካከል እንዳለው ሁሉ።

3.በመጀመሪያ አጋር ተመልሳ ሳራን ለጥቂት ጊዜ እንድታገልግል በእግዚአብሄር እንደተነገራት ህጉም ለአብርሀም ሰዎች እንደ ጊዜአዊ አገልግሎት የዚህ ምሳሌ ነበር።)

4.የተስፋው ዘር በተወለደ ጊዜ አጋርን ለማስወጣት ጊዜው እንደሆነ እግዚአብሔር ለአብርሀም ነገረው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ የሲናን ኪዳን ለማስወገድ ጊዜው ነበር፤ ግቡን መትቶ ነበር (ገላ 3፡24፣ 4፡3-5)።

ጌታ ኢየሱስ ያጋርን እና የሳራን ልጆች ያመለክታል። ዮሐ 8፡31-47

የአብርሀም ልጆች ነን ለሚለው ለአይሁድ ክርክር መልስ ኢየሱስ በስጋ የአብርሀም ዘሮች መሆናችሁ ልክ ነው ነገር ግን የአብርሀም መንፈሳዊ ልጆች አይደላችሁም ብሎ ይናገራል። የሀጢአት ባሮች፣ የዲያብሎስ ልጆች ነበሩ።

የአብርሀም ባሪያ - ልጅ ለዘላለም በቤት አልኖረም። እውነተኛው፣ የተስፋው ልጅ ነበር በቤት

የኖረው እና በእርሱ ነው ነጻነት የመጣው። ኢየሱስ ራሱ ነው እውነተኛው ልጅ እና የተስፋው ወራሽ የሆነው ሰዎችንም ነጻ የሚያወጣው።

የአብርሀም እውነተኛ ልጆች ልክ አብርሀም እንዳመነው እርሱን ያምናሉ ነጻም ይወጣሉ።

3ሐ ቁ 28-31 ላይ አሁን ለእኛ የአብርሀም ልጆች መንፈሳዊ ትርጉም

30.ከየትኛዋ እናት ወይም ኪዳን ጋር ነው የገላትያና ሁሉም ክርስቲያኖች መመሳሰል ያባቸው?

ከአሮጌው ኪዳን ጋር ሳይሆን ከሳራ፣ ከአዲሱ ኪዳን፣ ከሰማይ የህይወት ተስፋ ኪዳን ጋር መመሳሰል አለባቸው።

አሮጌውን ኪዳን አይንቁም፣ ከእግዚአብሄር እንደሆነ እና ለአዲሱ ኪዳን መምጣት ዝግጅት እንዳገለገለ ይረዳሉ።

አዲስ ኪዳን ስለመጣ ከአሮጌው ኪዳን በታች አይደሉም። አሮጌው አልፏል አዲሱ መጥቶአል!

ገላትያ 5

የምዕራፍ 5 ቅደም ተከተል

1 ህግ ሳይሆን ነጻነት፤ፈቃድ ሳይሆን ፍቅር	ሀ) ቁ 1 ግልጽ የሆነ አድርግና ግልጽ የሆነ አታድርግ
	ለ) ቁ 2-4 ወደ ህጉ አንድ ትንሽ ርምጃ፣ ክክርስቶስና ከጸጋ ትልቅ ማፈግፈግ ነው
	ሐ) ቁ 5-6 “በአዲስ ፍጥረት ግዛት” ውስጥ መኖር
2 የተሳተፉ ሰዎችና የተመለሰ ጥያቄ	ሀ) ቁ 7-12 ችግር ፈጣሪዎቹና የተቸገሩት የገላትያ ሰዎች
	ለ) ቁ 7-12 የጳውሎስ ውትወታ፣ ስብከት፣ ስደት፣ እና መሸት
	ሐ) ቁ 13-15 የክርስትና ህይወት ሊኖርበት የማይገባ መንገድ ፣ የክርስትና ህይወት መኖር

ገላትያ 5፡1-6 ህግ ሳይሆን ነጻነት፡፡ ፈቃድ ሳይሆን ፍቅር

1ሀ ቁ1. ግልጽ የሆነ “አድርግ” እና ግልጽ የሆነ “አታድርግ”

1) **በደብዳቤው ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ጳውሎስ ስለባርነት፣ ስለእስር፣ ስለነጻ መውጣትና ነጻነት እየጻፈ ነው፡፡**

የቀረውን ደብዳቤ ከመመልት፣ “ክርስቶስ እኛን ነጻ ያወጣን ለምን አይነት ነጻነት ነው”?

ክርስቶስ ከሚከተሉት ነገሮች ነጻ አውጥቶናል፡

- *ከዚህ ክፉ አለም (1፡3)*
- *ከአይሁድ የህግ ስርአትና ደህንነትን ከማያመጡ ሌሎች ህጎች (2፡4፣ 4፡25-31 እና 4፡8)*
- *አሮጌ ህወታችን በአሀጢትና በህግ ተገዝቷል ደግሞም ታስሯል (2፡17-21 እና 3፡21-23)*

ክርስቶስ ለሚከተሉት ነገሮች ነጻ አውጥቶናል፡

- *እንደማደጎ ልጆች በክርስቶስ ደስ እየተሰኘን ለእግዚአብር እንድንር 4፡5-7*

2) ክርስቲያኖችን እንዲያደርጉት ጳውሎስ የሚያዛቸው ምንድን ነው?

ጳውሎስ ክርስቲያኖችን የሚያዛቸው ክርስቶስ ላወጣቸው ነጻነት ጸንተው እንዲቆሙ ነው።።

ባሪያ ከሚያደርግ ከሀጢአት ሀይል በነጻነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ

- ✓ *ማዳን ከማይችል ለሀይማት ባሪያ ከሚያደርግ ህግ ጸንቶ መቆም*
- ✓ *በመንፈስ ቅዱስ ሀይል እንዳገኙ የእግዚአብሄር አብ ልጆ፣ በክረስቶ ባገኑት ርስት ወራሽነት ጸንቶ መቆም*

3)ክርስቲያኖች እንዳያደርጉ ጳውሎስ የሚያዛቸው ምንድን ነው?

ጳውሎስ እንደ ደህንነትና ለእግዚአብሄር የመኖር መንገድ ለየትኛውም የሀይማኖት ስርዓት እናዳይገዙ ይነግራቸዋል።።

በክርስቶስ ነጻ ወጥተናል ከህግም በታች ባሪያ መሆን የለብንም።።

1ለ. ቁ 2-4 ትንሽ ህጉን መከተል ከክርስቶስ ትልቅ ማፈግፈግ ነው፡

4)ጳውሎስ አጥብቆ የሚያስጠነቅቀው ሀይማኖታዊ ሥርዓት ምንድን ነው?

የመገረዝን ሀይማኖታዊ ስርዓት መቀበልን ጳውሎስ አጥብቆ ያስጠነቅቃል።።

5.ጳውሎስ እንዳይደረግ የሚያስጠነቅቀውን ግርዘት መቀበል አስከፊ ውጤቶች ምን ነበሩ?

አስከፊዎቹ ውጤቶች በክርስቶስ የሚገኙ በረከቶችን በሙሉ ማጣት እና ከክርስቶስ መለየት ናቸው።።

6.የመገረዝን መንገድ መከተል እንዲህ አይነት አስከፊ ውጤቶች የኖረው ለምንድን ነው?

ከሙሴ ህግ በታች ግርዛትን መለማመድ አንድን ሰው ሁሉንም የእግዚአብሄርን ህግ እንዲጠብቅ ያስገድደዋል።። ከህጉ በታች ደህንነትን ለማግኘት የምትሰራው ነገር ክፍል ነው (ሐዋ 15፡1 እና 5፣ ገላ 5፡3ለ)።።

በጣም አስከፊ ነበር የኢየሱስ ክርስቶስን መንገድ፣ እውነትና ህይወት መሆን መቃወም ስለሆነ።። የእግዚአብሄርን ጸጋ ውድቅ ማድረግና በራስ ጥረት የማይቻለውን የደህንነት ስራ መጀመርም ነው።።

1ሐ ቁ 4-5 "በአዲስ ፍጥረት" ክልል ውስጥ መኖር

በቁ 5 እና 6 አንድ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር የተቆራኘ እና በእግዚአብሔር ጸጋ ጸንቶ የቆመ መሆኑን ጳውሎስ ያሳያል።። የእርሱ መልእክት ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንን ከሀይማኖታዊው

ግዝረት ጋር አንድ እንዳያደርጉት የእግዚአብርንም ጸጋ ከሰው ጥረት ጋር አንድ እንዳያደረጉ ነው።

በቁ 5 እና 6 ላይ ክርስቲያች ክክርስቶ ጋር እንደተቆራኙ እና በእግዚአብሄር ጸጋ እንደሚኖሩ ሰዎች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ይገልጻል።

በቁ 5 ጳውሎስ ስለ ጽድቅ ተስፋ" ይናገራል።

<u>ይህ</u> ጽድቅን ስለማግኘት ተስፋ <u>አይደለም</u>። ስለጸደቁ የእነርሱ ሆኗል 2:15-16 እና 3:6-9። ይህ በርግጥ የክርስቶስ ጽድቅ ለተሰጣቸው ይህ ተስፋ የተደረገለት እና ቃል የተገባበት ነገር ነው።

7)ክርስቲያኖች የተረጋገጠ ተስፋቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ጳውሎስ 3 ነገሮችን ይነገራል፡

ሀ) ሀይልን የሚሰጣቸው ማን ነው?

ክርስቲያኖች ለህይወታቸው ሀይል የሚያገኙት በመንፈስ ቅዱስ ነው።

ለ)እንዴት ነው ሀይልን የሚሰጣቸው?

በክርስቶስ እምነት እንዲኖቸው በማድረግ መንፈስ ቅዱስ ሀይል ይሰጣቸዋል

ሐ)ያ የሀይል ስራ በተግባር የሚገለጠው እንዴት ነው?

በክርስቶስ ማመን በራሱ በክርስቲያን ፍቅር በተግባር ይገለጣል

2ሀ. ችግር ፈጣሪዎቹና የተቸገሩት የገላትያ ሰዎች

8.በቁ 7፣10 እና 12 ላይ በችግር ፈጣሪዎቹ ላይ የገላትያ ክርስቲያኖች ትኩረት ምን ላይ እንደሆነ ነው ጳውሎስ የሚናገረው?

በቁ 7 የሚያሰናክላቸውን ሰው እንዲለዩ የሚያደርግ ጥያቄን ይጠይቃቸዋል።

በቁ 10 ላይ የሚያስቸግራቸው ሰው ማን እንደነበር በመናገር ሰውየውን ያንላዋል። በቁ 12 ላይ ችግር ፈጣሪው ብቻውን እንዳልሆነ የሚሰራው ግልጽ ያደርጋል። የሌሎቹ ዋና መሪ ነበር።

9.በችግር ፈጣሪዎቹ አማካኝነት በገላትያ ሰዎች ላይ የሆነው ነገር ምንድን ነው ቁ 7?

በክርስትና ህይወት "በሚገባ በመሮጥ" ፈንታ አሁን በመጥፎ መንገድ እየሄዱ ነው። እያዘገሙና እየተደናቀፉ።

10.ችግሩን ባያስወግዱ ኖሮ የገላትያ ሰዎች ምን ይሆኑ ነበር ቁ 9?

ሙሉ በሙሉ ሁሉም ይጠፉ ነበር።

ልክ እርሾ ሊጡን በሙሉ እንደሚያቦካውና እንደሚለውጠው፣ ይህ የሀሰት ትርጉም በስተመጨረሻ ሁሉን ያበላሻቸው ነበር።

11.ቁ 8 ላይ ችግር ፈጣሪዎቹ (ጳውሎስ የማይሰብከውን) ግዘረትን በመስበክ የሚወተውቱ ነበሩ ቁ 11።

ስለስብከታቸው መነሻና እርሱን ስለመስበክ መነሻ ሃሳባቸው ጳውሎስ የሚናገረው ምንድን ነው?

መልእክታቸው የገላትያ ሰዎችን በክርስቶስ እንዲያምኑ ከጋዛቸው ከእግዚአብር እንዳልሆን ይናገራል።

መነሻ ሃሳባቸው ደህንነት በተሰቀለው ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ሰዎች ሲናገሩ የሚመጣውን ስደት ለማስወገድ እንደሆነ ይናገራል።

2ለ ቁ 7-12 የጳውሎስ ውትወታ፣ ስበከት፣ ስደትና ምኞት

12.ጳውሎስ እርግጠኛ የሆነበት ነገር ምን ነበር ቁ 10?

1)ቁ 10ሀ ላይ ጌታ የገላትያን ሰዎች ከነበሩበት አደጋ ሊያድናቸው እንደሚችል እርግጠኛ ነበር

2)የገላትያ አማኞች እርሱ የያዘውን ምልከታ እንደሚይዙ እርግጠኛ ነበር። ግርዘት፣ ለህግ ከመታዘዝ ባርነቱ ጋር፣ ወይም ምንም አይነት ሌላ ወንጌል ወደፊት የሚወስድ መንገድ አይደለም። የመስቀሉ ቃል ብቻ ነው የህይወት መልእክት።

3) የመስቀሉን ቃል በመቃወም ልዩ ወንጌል የሚሰብኩ ሰዎች ሳይቀጡ አይቀሩም።

13) ለምንድን ነው ጳውሎስ የሀሰት አስተማሪዎቹ ሙሉ አካላቸውን እንዲቆርጡና ራሳቸውን በመግረዝ ብቻ እንዳይቆሙ የሚሻው?

ይህ አስቸጋሪ ጥቅስ ነው ደግሞም የተለያዩ ትርጉሞች አሉት። ምናልባት የጳውሎስ ትርጉም "በግርዘት ወንጌል የሚያስቸግሩአችሁ እነዚህ ሰዎች፣ የሀሰት ሀይማኖቶች የሚያደርጉትን እንዲያደርጉ ራሳቸውን እንዲሰልቡ እሻለሁ፣ በዚያ መንገድ ለማንም ሰው ይህ የሀሰት ወንጌል እንደሆነ ግልጽ ይሆናል"።

ትክክለኛው ትርጉም ምንም ይሁን ከእነዚህ ከሀሰት አስተማሪዎች ጋር ያለ ግንኙነት ሁሉ እንዲቆረጥ ይፈልጋል።

2ሐ ቁ 13-15 የክርስትናን ህይወት እንዴት ነው መኖር የሌለብን እና ያለብን?

የግርዘት አስተማሪዎች ጳውሎስ የሰበከውን ወንጌል መከተል ሰዎች ስለሀጢአት በቸልታ እንዲኖሩ ያደርጋል ብለው ያምናሉ። መንፈሳዊ ህይወት የመኖሪያ ብቸኛው መንገድ በወንዶች መገረዝ በሚጀምር በእግዚአብሄር ህግ ስር መኖር እንደሆነ ይሰማቸዋል።

ሀ) ለእግዚአብሄር ህግ ቀጥታ በመገዛት ማንም ሰው መንፈሳዊ ህይወት መኖር እንደማይችል

ለ) ወንጌል በትክክል ሲረዱት ማንንም ሰው ስለሀጢአት ቸል እንዲል አያደርገውም ይልቁን ስለቅድስና የበለጠ ግድ እንዲላቸው ያደርጋል ቅዱስም እንዲሆኑ ሀይል እንደሚሰጣቸው ጳውሎስ አጥብቆ ይናገራል።

14)ጳውሎስ የገላትያ ሰዎችን እግዚአብሄር በወንጌል ሲያድናቸው / ሲጠራቸው ከሀጢአት ባርነት እና ከህግ ስርአት ነጻ እንዳወጣቸው ያስታውሳቸዋል (ቁ 13 እና ቁ 1-3)።

ከህግ ነጻ ስለወጡ እንዳያደርጉት ጳውሎስ የሚጠይቃቸው ነገር ምንድን ነው ቁ 13?

እግዚአብሄር ከህግ ስርዓት ነጻ ስላወጣቸው የወደቀውን የሐጢአት (የስጋ) ማንነት በመታዘዝ ለመኖር እንዳይጠቀሙበት አጥብቆ ይነግራቸዋል።

15)እንዴት ነበር መኖር የነበረባቸው ቁ 13?

ለሚያገለግል ፍቅር የተሰጠ አቅጣጫን በመታዘዝ ነው መኖር የነበረባቸው።

16) በሚያገልግል ፍቅር እየተመራ ህይወት ሲኖር መንፈሳዊ ህይወት ያለመኖር አደጋ የማይኖረው ለምድን ነው ቁ 13-14?

የሚያገለግል ፍቅር ህግ የሚጠይቀውን ነገር ሁሉ ስለሚያረካ ነው።

17) ወንጌል በሚደግፈው ፍቅር ቁጥጥር ስር ከመሆን ይልቅ ህግ በሚለው የራስ ጽድቅ ቁጥጥር ስር ሰዎች ሲወድቁ ብዙ ጊዜ የሚሆነው ነገር ምንድን ነው ቁ 15?

ሰዎች አንዱ በሌላው ላይ ይነሳል፣ መተቸት፣ መኮነን፣ ስህተት መፈለግ፣ ሁልጊዜ የበላይነት ይሰማቸዋል።

መንፈስ ስጋ ህግ

3ሀ ቁ 16-23 ውጊያው የት ነው ያለው እንዴትስ ነው ድል የሚደረገው?

18) “በመንፈስ ለመመላለስ” ቁ 16 ወይም “በመንፈስ መመራት” ቁ 18፣ አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስ ሊኖረው ይገባል።

በዚህ ደብዳቤ አማኞች በውስጣቸው ሊኖር መንፈስ ቅዱስ እንደተሰጣቸው ለገላትያ ሰዎች የጻፈላቸው እንዴት ነው?

ጳውሎስ ይህን የጻፈው፡

- ✓ *በ3፡2-3 ውስጥ በክርስትና ህይወታቸው ጅማሬ ላይ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነበር*
- ✓ *3፡14 ውስጥ ክርስቶስ ስለእኛ እርግማ ሆኗል ስለዚህ በእርሱ ያመንን እኛ ተስፋ የተገባውን መንፈስ ቅዱስ መቀበል እንችላለን*
- ✓ *4፡6 በደህንነት ልጅ ለሆኑት ሁሉ እግዚአብሄር የልጁን መንፈስ ወደልባቸው ይልካል*

19) አማኝ የማያምን ሰው የሌለው ውስጣዊ ጦርነት ይኖረዋል። ለምንድን ነው ይህ የሚሆነው ቁ 17?

አማኝ አማኝ ያልሆነ ሰው የሌለው ውስጣዊ ጦርነት ይኖረዋል። ይህ የሚሆነው በክርስቲያን ውስጥ የሚኖረው ስጋዊው ወይም የወደቀው የሰው ማንነት በአዲስ ማንነታቸው እና በውስጣቸው እንዲኖር እግዚአብሄር በሰጣቸው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ስለሚነሳ ነው።

20) በገላትያ ሌላ ቦታ ውስጥ የቱጋ ነው ከመንፈስና ስጋ ንጽጽርና ግጭት ጳውሎስ የጻፈው (ጥቅሶቹን ስጥ)።

ጳውሎስ ስለዚህ የፃፈው በ3፡3፣4፡23 እና 4፡29 ውስጥ ነው።

22) ከቀደሙት ጥቅሶች (5 እና 6) "በመንፈስ የምንመላለሰው" እንዴት ነው ቁ 16።

- *በእምነት በመንፈስ እንመላለሳን ቁ 5*
- *በክርስቶስ ያለ ያ የእምነት ልምምድ በፍቅር ራሱን ይገልጣል ቁ 6*
- *ያ ፍቅር ሌሎችን በማገልገል ራሱን ይገልጣል (ቁ 13)*

21) በክርስቲያኖች ውስጥ የማያቋርጥ ውጥረት የሚኖረው ለምንድን ነው ቁ 17?

የማያቋርጥ ውጥረት የሚኖረው ል በርብቃ ማህጸን ውስጥ ሁለቱ ህዝቦች (ዘፍ 25፡22-23)፣ በአማኙ ህይወት ውስጥ ሁለት መንግስቶች አሉ፣ የስጋ መንግስትና የመንፈስ መንግስት፣ የአማኙን ፈቃድ ለማሸነፍ በመታገል።

23) በመንፈስ የሚመላለስ አማኝ መገለጫው ምንድን ነው ቁ 16?

በመንፈስ የሚመላለስ አማኝ በስጋው ሳይሆን በመንፈስ ይመራል። መላው ባህሪና አመለካከቱ የተቀደሰ ይሆናል ምክንያቱም በውስጥ ትግል ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይሰማል የስጋውን ሳይሆን።

24) በመንፈስ የመመራት ጽኑ ዋስትና ምንድን ነው ቁ 18?

በመንፈስ የመመራት ጽኑ መልእክት ሰውየው በህግ ስር አለመሆኑ ነው።

ይቅር ተብሏል፣ ልጅ ተደርጓል፣ የእግዚአብሄር ቤተሰብ አባልም ሆኗል ሮሜ 8፡1-17

መንፈስ ስጋ ህግ

3ለ ቁ 19-23 የስጋና የመንፈስ ህይወት ንጽጽር

25) ደህንነት በጻጋ ነው የሚለው ላይ የሀሰት አስተማሪዎች ትችት ሰዎች የሀጢአት ህይወት ይኖራሉ የሚል ነው።

26) በሀጢአት ላለመኖር ብቸኛው መንገድ ምንድን ነው ቁ 22-23?

በሀጢአት ላለመኖር ብቸኛው መንገድ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬን ለማፍራት ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ መመራት ነው፡

27) በክርስቲያኖች ህይወት ህጉ ሪደንደንት የሚሆነው ለምንድን ነው ቁ 23?

ህጉ በክርስቲያኖች ህይወት ሪደንደንት የሚሆነው መላው ህይወታቸው አሁን በመንፈስ ቅዱስ መመራት ስላለበት ነው።

ህጉ የሚኮንነው ወይም የሚገስጸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ምንም የለም፣ ዝም ነው ያለው።

ሮሜ 8፡1-6ንም ተመልከት።

28) "ስለ ስጋ ስራዎች" ሲናገር ጳውሎስ ብዙ ቁጥር "ስለመንፈስ ፍሬ" ሲናገር ደግሞ ነጠላ ቁጥር የሚጠቀመው ለምንድን ነው?

"በስጋ ያሉት" ገና በክርስቶስ ነጻ ያልወጡ ሰዎች እንደ አዛዥ ጌታ "የስጋ ማንነት" ነው ያላቸው። ሁሉን አይነት የስጋ ስራዎች ለማግኘት እየሰሩ አይደለም። ሀጢአቶቻቸው ብዙውን ጊዜ በጥቂት የስጋ ስራዎች የተካኑ ናቸው።

"በመንፈስ" የሆኑት "በመንፈስ የሚመላለሱት" ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ሙሉ ፍሬን ማፍራት አለባቸው። ወጥነት ያለው ፍሬ ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን ወጥነት ባለው ውበቱ የመንፈስ ፍሬን ለማፍራት የተካነ መሆን አለበት።

መንፈስ ስጋ ህግ

3ሐ. ቁ 24-26 የተሰቀለው ስጋ። በመንፈስ ህያው የሆነ። መንፈሳዊ ትምክህት የለም።

29) "በመንፈስ ቅዱስ መኖር" ሲል ጳውሎስ ምን ማለቱ ነው ቁ 25?

መልሱ ከ6-14-16 ጋር መገናኘት አለበት።

ለስጋ አገዛዝ በመመሞት፣ አማኞች ዳግም እንደተወለዱ ህዝቦች ለመንፈስ ቅዱስ አገዛዝ መኖር አለባቸው ማለቱ ነው።

2 ቆሮ 5፡17 እና ሮሜ 8፡2ን ተመልከት።

30) ቁ 25 ላይ ጳውሎስ "መንፈስን ጠብቁ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

መንፈስን መጠበቅ ማለት፡

የራሱን መንገዶች በመከተል መገሰስገስ ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ከፍ ሲያደርገው ቀና ብሎ ክርስቶስን ማየት እና መንፈስ ቅዱስ በቃሉ ለእኛ እርሱን በሚያሳይበት ሁኔታ ወደ ክርስቶስ መልእ መለወጥ።

31) መንፈሳዊው ትምክህት ህግ አጥባቂ ሰዎች ብቻ የሚቸገሩበት ነገር አይደለም፤ የመንፈስ ቅዱስን ስራ የሚለማመዱ ክርስቲያኖች መካከልም በሽታ ሊሆን ይችላል።

በቁ 26 ውስጥ ጳውሎስ ክርስቲያኖች እንዲያደርጉአቸው የሚያስጠነቅቃቸው 3 ነገሮች ምን ምን ናቸው?

1. *በመንፈሳዊ ልምምዳቸው ትምክህተኞች እንዳይሆኑ*
2. *በመንፈሳዊ ህይወታቸው ሌሎችን ለማስቀናት እንዳይሞክሩ*
3. *ሌሎችን ማየትና መንፈስ ቅዱስ በህይወታቸው እያደረገ ባለው ነገር እንዳይቀኑ ክርስቲያኖችን ጳውሎስ ያስጠነቅቃል።*

ገላትያ 6

የምዕራፍ 6 ቅደም ተከተል

1.የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ህይወት ገላ 6፡1-10

1ሀ ቁ 1-2 ስለሌሎች መንፈሳዊ ጤንነት እና ቅድስና መጠንቀቅ

1.ክርስቲያኖች "ህግ መጠበቅ" እንዳለባቸው የሚገፋፉ ሰዎች በፈተና ተጠምዶ ባገኙት ማንኛውም ሰው ላይ ጨካኝ ሆነው የነበረ መሆን አለበት::

ከቁ 1-2 ውስጥ በሀጢአት ለወደቁ አማኞች ክርስቲያኖች ሊያሳዩት የሚገቡ 3 ነገሮች ምን ምን ናቸው?

በሀጢአት ለወደቀ አማኝ ትክክለኛ ክርስቲያን ሊያሳያቸው የተገቡ በቁ 1-2 ውስጥ ያሉ ነገሮች፡

1) *በቁ 1 ላይ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን "ወንድሞች" ብሎ ይጠራል፣ ይህ ሁላችንም የክርስቶስ "ቤተሰብ" መሆናችንን የማመላከቻ መንገድ ነው::*
2) *"በየዋህነት መንፈስ" ለማዳን መምጣት አለብን ቁ 2::*
3) *ሌላውን ሰው እየሰበረ ያለውን በመሸከም መረዳትና የክርስቶስን ህግ፣ ፍቅርን መፈጸም አለብን (ዮሐ 13:24)*

ማስታወሻ፡ በቁ 1 ውስጥ "መያዝ" የሚለው ቃል በሚከተሉት አጀንዳ ሊሆን ይችላል፡

- *በፈተና ወጥመድ መጠመድና በርሱ መያዝ ወይም*
- *ሀጢአት በሚያደርግ ጊዜ በሌሎች ክርስቲያኖች መያዝና መገኘት*

የመጀመሪያው ትክክል ይመስላል ምክንያቱም

ሀ. ጳውሎስ ሁሉንም ሰው የመንፈስ ፍሬን በማፍራት በመንፈስ እንዲመላለስ እየመከረ ነው፤ 5:16 እና 22::

ለ. ቁ 1 ውስጥ "መተላለፍ" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል "መውደቅ"፣ "የተሳሳተ ርምጃ" "ማዳለጥ" ወይም " መንሸራተት" ማለት ነው ::

ሐ. "መመለስ" የሚለው ቃል በድብቅ ሀጢአት ያደረገ እና ገና በቅርብ ጊዜ "የተያዘ" እና የተገኘ ሰውን ሳይሆን ድንገት የወደቀ ሰውን ይጠቁማል::

2."በምንም አይነት ሀጢአት መያዝ" የሚለው አባባል ስለ ፈተና ምን ይግረናል?

ይህ ፈተናዎች ባልተጠነቀቅን ጊዜ እንደሚያስደነግጡንና እንደሚይዙን ይነግረናል::

የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለመከተል እየሞከርንም ቢሆን እንኳን::

3.ጳውሎስ "እናንተ መንፈሳዊ የሆናችሁ" የሚላቸው እንማን ናቸው?

ጳውሎስ በመንፈስ የሚመላስ እና በሚያዳልጥ በፈተና መንገድ ያለፈና መርዳት የሚችል ማንኛውንም ክርስቲያን ወንድም ወይም እህት ማለቱ ነው::

ማስታወሻ፡ “መመለስ” የሚለው ቃል የሰተበረ አጥንትን ለመመለስ በሚደረግ እንክብካቤ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል። እንደገና በትክክለኛ ቦው ላይ መመለስ።

4.እርስ በርስ ባለን እንክብካቤ ውስጥ የመጨረሻው ግባችን ምን መሆን አለበት? ቁ 1

ለአጠቃላዩ የክርስቲያን ማህረሰብ ዘላቂ ግባችን የእያንዳንዱ አባል መንፈሳዊ ጤንነት እና ቅድስና ው።

5.ሌሎች ከሀጢአት እንዲመለሱ በመርዳት ጊዜ ክርስቲያኖች ስሚያስፈልጋቸው የዋህነት እና ጥንቃቄ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች ክፍሎችን መዘርዘር ትችላለህን?

ዕብ 5፡1-2

ማቴ 5፡7

ያዕ 2፡13

ያቆ 4፡7-12

ማር 14፡34-36

1 ቆሮ 10፡12-13

1 ጴጥ 5፡5-11

ማስታወሻ፡ በቁ 2 ውስጥ “ሸክም” እና በቁ 5 “ጭነት” የሚሉት ቃላት ሁለት የተለያዩ የግሪክ ቃላት ናቸው። የመጀመሪያው አንድ ሰው እርዳታ የሚሻበት የሚሰባብር ሸክም ሲሆን ሁለተኛው ልክ እንደ ጀርባ ሸክም በአንድ ሰው ለመሸከም የተመቻቸ ጭነት ነው።

6.ቁ 2 ከቁ 1 የቀጠለ እንደሆነው ሁሉ፣ ጳውሎስ ምን አይነት “ሸክም” ነው በሃሳቡ ውስጥ ያለው?

በሀጢአት የመውደቅ የጥፋተኛነትና የሀፍረት ሸክም መሆን አለበት ጳውሎ እያለ ያለው። ስንወድቅ በትክክል በህሊናችን ላይ መክበድ አለበት። የሰተሰበረ እና የደቀቀ ልብን እግዚአብሄርም ሆነ ክርስቲያን ወገኖች አይንቁም።

እግዚአብሄር ሰባራውን ልብ ይጠግናል።

ማስታወሻ፡ *“ስለዚህ የክርስቶስን ህግ ፈጽሙ” በማለት ጳውሎስ “የሙሴን ህግ ፈጽሙ” የሚለውን እያነጻጸረ ይሆናል። የክርስቶስ ህግ ፍቅር ነው።*

1ለ ቁ 3-5 ስለራሳችን መንፈሳዊ ጤንትና ቅድስና መጠንቀቅ

7.በስጋ ለሚመሩ ሰዎች በሀጢአት ስለወደቁ ሰዎች ሲሰሙ የበላይነት መሰማት በጣም ቀላል ሊሆን ይችላል።

በቁ 3 ውስጥ እንደዛ ስለሚያስብ ሰው ጳውሎስ የሚናገረው ምንድን ነው?

ጳውሎስ እንደታለሉ ይናገራል፣ "የበላይነት ሰሜታቸው" ምንም የሌለ እንደሆነ ይናገራል።

8.ቁ 4 ላይ እንድናደርገው ጳውሎስ የሚነግረን ምንድን ነው?

ራችንን ከሌሎች ጋር በማወዳደር ራሳችንን እንዳናጸድቅ ጳውሎስ ይነግረናል።

በእግዚአብሄር ፊት ራሳችንን መመርመር አለብን (1 ቆሮ 11:28፣ 2 ቆሮ 13:5-6፣ ዮሐ 21:20-22 እና ሮሜ 12:3)።

9)ቁ 5 ላይ ያንን እንድናደርግ የሚነግረን ምንድን ነው?

በፍርድ ቀን እግዚአብሄር በህይወት ዘመናችን እንዳናደርገው አደራ ለሰጠን ነገር ሁሉ በየግል ለእግዚአብሄር ምላሽ መስጠት ስላለብን ነው ይላል ጳውሎስ (2 ቆሮ 5:10)

1ሐ ቁ 6-10 ለሁሉም ጥቅም መንፈሳዊ ነገሮችን ኢንቨስት ማድረግ

10)ስለማጨድና ስለመዝራት ስንት ጊሴ ነው በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ጳውሎስ የሚጽፈው?

ጳውሎስ 3 ጊዜ እንደዚህ ይጽፋል

መዝራትና ማጨድ ቁ 7 ውስጥ

በስጋ ወይም በመንፈስ ስለመዝራት ቁ 8

ማጨድ በቁ 9 ውስጥ

ማስታወሻ፡ *ዘርን መዝራት የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት ነው*

በመጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ዘርን መዝራት መንፈሳዊ እውነታዎችን ለማመላከት ጥቅም ላይ ውሏል።

- *"የዘራኸውን ታጭዳለህ" ኢዮብ 4:8 እና ሆሴዕ 8:7ን ፣ 1 ቆሮ 15:37-38፣ ማቴ 7:16 እና ያቆብ 3:18ን ተመልከት*
- *"በዘራህበት መንገድ ታጭዳለህ" 2 ቆሮ 9:6*
- *"ከዘራህ ከረጅም ጊዜ በኋላ ታጭዳለህ" ያቆብ 5:7-8*
- *"ጌታ ኢየሱስ በምሳሌዎቹ ውስጥ ዘር መዝራትን እንደ ምሳሌ ጥቅም ላይ አውሏል፣ ማቴ 13:3 እና 27።*

11. ስለምን አይነት "በመንፈስ መዝራት" ወይም በመንፈሳዊ ነገሮች ላይ ኢንቨስት ስለማድረግ ነው በቁ 6 ጳውሎስ እየጠቆመ ያለው?

ክርስቲያኖች አንዱ "በመንፈስ የሚመላለሱበት" መንገድ (5:25) የእግዚአብሄር ቃል የሚያስተምሩትን በመደገፍ እንደሆነ ይናገራል። ቁሳዊ በረከቶችን የእግዚአብሄርን ቃል ለማስተማር ከሚተጉ ሰዎች ጋር በመካፈል ይህንን ማድረግ ይችላሉ።

1 ቆሮ 9:3-12 በተለይ ቁ 11ን

ሉቃስ 10:7 እና 1 ጢሞ 5:17-8

(ሮሜ 15:27) ንም ተመልከት

12. ይህ ሰባኪዎችን መደገፍ ስለማስተማር ስራና እንዴት ለነእርሱ ዋጋ መስጠት ስላለብን መንገድ ምን ይነግረናል?

በሌላ ስራ ለኑሮአቸው የሚሆነውን ለመስራት ጊዜ እስከማይኖራቸው ድረስ፣ ማስተማር የአስተማሪውን ብዙ ጊዜና ሀይል የሚወስድ መሆን አለበት።

የእግዚአብሄርን ቃል ለማስተማር ሙሉ ትኩረታቸውን እንዲሰጡ እነርሱን በመክፈል ከሌላ ስራ ነጻ ለማድረግ ለስራቸው በጣም ዋጋ መስጠት አለብን። (ሐዋ ስራ 6:2-7)።

13.አንዳንዶች በሰባኪዎችና ለእግዚአብሄር በሚሰሩ ላይ "ሊዘብቱ" ሊያደርጉ ይችላሉ ነገር ግን ቁ 7 ላይ ጳውሎስ የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

ጳውሎስ እግዚአብሄር አይዘበትበትም ብሎ ያስጠነቅቃል። በእርሱ ላይ የዘበቱ ቁጣውን ያጭዳሉ።

14. ገበሬ በድንገት ዘር አይዘራም ፤ ከመዝራት ጀርባ እሳቤና ዝግጅት አለ።

በስጋ ለመዝራት እራሳችንን በሞኝነት የምናዘጋጀው እንዴት ነው?

ሮሜ 13:14ን አንብብ

በሞኝነት፡

በፈተና ስፍራ እንቆይ ይሆናል ወይም ሆነ ብለን ለፈተና እንጋለጣንለን።

(ኢዮብ 31 ነገር ግን ስለዳዊትና ቤርሳቤህ አስብ)

እንዲህ ያሉ ሀሳቦችን በመስቀል ፈንታ ቅናትና ቁጣን እናሳድጋን (ኤፌ 4:26)

ከሚያበላሹን ሰዎች ጋር ህብረትን እንፈጥራለን 1 ቆሮ 15:33

(መዝ 1:1 - ጴጥሮስና ክህደቱን አስብ)።

መዋሸት የአንዳንድ ሀጢቶችን ዕቅድ ያነሳሳል ሚክያስ 2:1-2።

እርሱን ከማስወገድ ይልቅ ባለፈው የፈተንነን ነገር ማቆየት።

15.በመንፈስ ለመዝራት በጥበብ የምንዘጋጀው እንዴት ነው?

ሮሜ 8:5-17ን አንብብ

ሮሜ 8፡7-8 እርሱን ደስ ማሰኘት በመፈለግ፣ ለራሳችን ጥቅም ሳይሆን ለእግዚአብሄር ደስተኛ፣ ትሁት፣ ታዛዥ እና የሚገዛ ልብ ሊኖረን እንደሚገባ እናያለን።

- *ሮሜ 8፡13-14 እና 12፡1-2 በብልቶቻችን ውስጥ ከሚሰራው ሀጢአት ጋር እስከሞት ድረስ ትግል እንዳለን ያሳያል*
- *ሮሜ 8፡15-16 ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህብረት የማድረግ ልማድ እንደሚያስፈልገን እና ወደ አብ አባ አባ ብለን የምንጮህበትን ርዳታ መፈለግ እንዳለብን ያሳያል።*
    - ✓ *መንፈስ ቅዱስ እንደተሰጠን ከእግዚአብሔር ቃል ደግሞም እርሱን ለማስተማር ካስታጠቃቸው ሰዎች ተማር (ገላ 6፡6)*
    - ✓ *እምነት ካላቸው ሰዎች ጋር ወዳጅነትን መስርት (ዕብ 10፡24-25)*
    - ✓ *በብርታቱ ሀይል ቅድስናን ተከታተል (ዕብ 12፡14)*

16. በስጋ የመዝራትና በመንፈስ የመዝራት ተቃራኒ ውጤቶች ምን ምን ናቸው?

በስጋ መዝራት በአሁን እና በዘላለም ውስጥ መበስበስን ያመጣል

በመንፈስ መዝራት በአሁን ንጽህና፣ ደስታ እና ከእግዚአብሄር ጋር ህብረት ማድረግን፣ በሚመጣው ህይወትም ዘላለማዊ በረከትን፣ የዘላለም ህይወትን ያስገኛል (ዮሐ 17፡3)።

17.እነዚህ ወሳኝ መከሮች ከአሁን ጀምሮ እስከ ወደፊት በመንፈስ የምትዘራበትን መንገድ ላይ ተጽኖ የሚያደርጉት እንዴት ነው?

....

....

....

....

18. ቁ 9ን በማንበብ፣ "የመንፈስ ኑሮ" ሁልጊዜ በልእለ ሀይል ስሜት መኖር፣ ቶሎ ቶሎ ለውጥ የማየት እና ፍጹም ያለመውደቅ ስሜት ነውን?

አይደለም።

ሀ) በመንፈስ መኖር ማለት እስከማይደክመን ዘላቂ ሀይል አለን ማለት አይደለም (ኢየሱስ ታክቶት እንደነበር አስታውስ)።

ለ) ትዕግስት እስከማያስፈልገን ድረስ ሁልጊዜ ቶሎ ቶሎ ለውጥ እናገኛለን ማለት አይደለም (ትዕግስት ከመንፈስ ፍሬ አንዱ እንደሆነ አስብ)።

ሐ) በፍጹም ተስፋ አንቆርጥም ማለት አይደለም (ሙሴን፣ ኤልያስን እና ጳውሎስን አስታውስ)።

በመንፈስ ቅዱስ መኖር ማለት ከድካማችን ምንም በጎ ነገር የሌለ ሲመስለንም እንኳን መልካም እያደረጉ በጸጋ መኖር ማለት ነው።

19. "መልካም ነገሮችን ለማድረግ ባለመድከም" ቁ 9 በመንፈስ መዝራት ማለት በተግባር ምን ይስላል (ቁ 10) ?

አንድ አማኝ መልካም ለማድረግ አጋጣሚዎችን እንደሚፈልግ እና እንደሚጠቀምባቸው አድርጎ ራሱን ያያል። የሚረዱት ሰዎች አማኞች መሆን አለመሆን ዋና ነገር አይደለም፤ ምንም እንኳን መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ያሉ ወንድሞችን እና አህቶችን መርዳት ልዩ ትኩረት እንዲኖረን ቢፈልግም እንኳን።

2.የትምክህት የተሻሉና የከፉ አይነቶች

2ሀ ቁ 11-12 ጳውሎስ ራሱን ከሀሰተኛ አስተማሪዎች ጋር ያነጻጽራል

20 ለምንድን ነው ጳውሎስ ለእነርሱ እየጻፈ ማመላከትና በትላልቅ ፊደላት መጻፍ ያስፈለገው? ቁ 11

(መልሱ ከ4፡13-17 እ ከቁ 12 ጋር የተገናኘ ነው)።

ጳውሎስ መጀመሪያ ለእነርሱ የሰበከበትን ጊዜ ያስታውሳቸዋል። በእይታው ያኔ ይቸገር እንደነበር አሁንም ይቸገራል እነዚህን የመዝጊያ ንግግሮች ሲጽፍም አንኳን።

ካለመቻሉ ጋር ለመጻፍ ባደረገው ጥረቱ፣ በራሱ ለእነርሱ ለመጻፍ እስክርቢቶ እንደያዘ እንዲያውቁ ፈልጓል።

ከዚህ እውነታ የገላትያ ሰዎች ጳውሎስ ምንም በስጋው የሚያበራ ወይም የክብር የሆነ ነገር ባይኖረውም ለእነርሱ ያለው መንፈሳዊ እንክብካቤ ጥያቄ ውስጥ መግባት እንደሌለበት እንዲያስቡ ተደርገዋል።

የግርዘት ቡድኖች በፍፁም እንደዛ አይጽፉም። ጽፈው የሚያውቁም ከሆነ በማራኪ የእጅ ጽሁፍ መጻፋቸውን ያረጋግጣሉ።

ለገላትያ ሰዎች ስለሚገዳቸው የሚጽፉ አይመስልም የገላትያ ሰዎች እንዲያሞጋግሷቸው ብቻ ነው የሚፈልጉት።

2ለቁ12-13 የግርዘት ቡድን ፍርሀትና ግብዝነት

21 የግርዘት ቡድን ሰዎች ስለገላትያ ሰዎች መገረዝ እንዲህ የቀኑት ለምን ነበር ቁ 12?

ሰዎች እንዲገረዙ በማድረግ ከአይሁድ ሀይማኖት ጥበቃ በስተጀርባ ለመደበቅና ከተሰቀለው ክክርስቶስ ወንጌል የሚመጣውን ስደት ለማስቀረትይችላሉ።

22. የግርዘት ቡድን የክርስቶስን የመታመን የወንጌል መልእክትን ብቻ ለደህንነት ማመን ሀጢአትን ያበረታታል ይላሉ ስለዚህም ክርስቲያኖች ከሙሴ ህግ ስር እንዲሆኑ ይገፋፋሉ፡፡ ስለዚህ የእነርሱ ህይወት ህግን የመታዘዝ ድንቅ ምሳሌዎች ነበረን ቁ 13?

አልነበረም፡፡ የእነርሱ ህይወት ክክርስቲያኖች ይልቅ የተቀደሰ አልነበረም፡፡ ሰዎች መገረዝ እና ህጉን መጠበቅ አለባቸው የሚለው ክርክራቸው የግብዝነት ነበር፡፡

2ሐ ቁ 14-15 በመስቀሉና በአዲስ ማንነት መመካትና

23 የግርዘት ሰባኪዎች ስለገላትያ ሰዎች መገረዝ እንዲህ የቀኑት ለምን ነበር ቁ 13?

ለስርአቱ እንዲገዙ ባሳመኑአቸው ቁጥሮች መመካት ስለፈለጉ ብቻ ነው፡፡ ለህይማኖታዊ ቅናታቸውና ስኬታቸው እያንዳንዱ እንደሌላ የስኬት ምርኮ ይታይ ነበር፡፡

24 ጳውሎስ ሊመካበት የወደደው አንድ ነገር ምንድን ነው?

ጳውሎስ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ነው መመካት የፈለገው

25 ጳውሎስ "አለም ለእኔ ተሰቅሏል እኔም ለአለም ተሰቅያሁ" ሲል ምንማለቱ ነው ቁ 14?

መሰቀል ወሳኝ የሆነ ፍጻሜ ነው፡፡ ከርግማን በታች የሆነ ሞት ነው፡፡ በተሰቀለው ክርስቶስ በመታመን ጳውሎስ አለም ከሰይጣን ህግ በታችና ከርግማን በታች እና ከእግዚአብሄር ፍርድ በታች እንደሆነች ይመለከታል፡፡ "ይራቅ፣ በእኔ ላይ አይገዛም!" አለ፡፡ በእርሱ ላይ የእርሱን መንገድና አገዛዝ በተመለከተ እንደተሰቀለ ቆጠረው፡፡ አለም ጳውሎስን ተመልክቶ ሙሉ በሙሉ ከኢየሱስ ጋር ተስተካክሎና ተመሳስሎ ያየዋል ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳደረገው ያደርገዋል፣ እንደተረገመ፣ እደተፈረደበትና እንደተሰቀለ፡፡

ከርሱ ጋር ምንም ነገር የለኝም፡፡

26.የአለም ስብከትና በጳውሎስ ላይ ገዢ መሆን በመስቀሉ ስላበቃ እና በመስቀሉ ምክንያት አለም ከጳውሎስ ጋር ምንም ጉዳይ ስለሌለው ጳውሎስ ለምንድን ነው መኖር የነበረበት ቁ 15?

ጳውሎስ የሚኖለት አዲስ የሆነ ምዕራፍ አለው፣ ከእግዚአብሄር ጋር የሆነ የወደፊት፡፡ በክርስቶስ መስቀል ከሀጢትና ከሞት በታች ካለ ህይወት ተለይቶአል፡፡ በአዳም ከወደቀው ከአለም ጋር ያ ግንኙነትን አብቅቶአል ደግሞም ከሞት ከተነሳው ጌታ፣ ከፍጥረት በኩር ጋር

ባለ ህብረት ተተክቷል። ከሀጢትና ከሞት በላይ በሆነ ከእግዚአብሄር ጋር ባለ የአዲስ ፍጥረት ህይወት ተተክቷል።

ወደዚህ አዲስ ፍጥረት ነው በክርስቶስ ያመነ ማንኛውም ሰው የገባው።

ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው 2 ቆሮ 5፡17

በክርስቶስ ኢየሱስ ላለ አዲስ ህይወት በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ተወልደዋል።

3.ማጠቃለያ

3ሀ ቁ 15-16 በአዲስ ፍጥረት አስደናቂ እውነታ መኖር

27.የግርዘት ቡድን በህግ ስርዓት የሚኖሩ ሰዎች ይኖረዋል (5፡3፣ ሐዋ ስራ 15፡5)፣ አማኞች በምን "ህግ" እንዲኖሩ ነው ጳውሎስ የሚናገረው ቁ 15-16?

ክርስቲያኖች መላ ህይወታቸውን ሊመሩበት የተገባ ህግ ወይም መርህ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የመሆን እውነታ እንደሆነ ጳውሎስ ይናገራል።

28. በ2፡20 የጳውሎስ ምስክርነት በዚህ ህግ መኖር በተግባር ምን እንሚመስል ይነግረናል።

በ2፡20 የማን ህይወት ነው በጳውሎስ እየተኖረ ያለው? እንዴት?

የአዲስ ፍጥረት ህይወት ከሞት የተነሳው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት ነው። በሁሉም ክርስቲያን ውስጥ እና በጳውሎስ በኩል ይኖራል።

በሚያስበው፣ በሚኖረውና በሚያደርገው ሁሉ ኢየሱስን በማየት እያንዳንዱ ክርስቲያን ይህንን ህይወት በእምነት ይኖራል።

ማስታወሻ፡ "በእግዚአብሄር እስራኤልም ላይ" ሲል ጳውሎስ አይሁድን እንደ ህዝብ ማየት የሌለብን በቂ ምክንያቶች አሉ።

1. ከግርዘት ቡድኖች በላይ "አይሁድ" ማነው? ቢሆንም ግን በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ሁሉ በእነርሱ ህይማኖት ጸጋና ሰላም ሊኖር እንደማይችል ጳውሎስ እያስረዳ ነው።

2.የገላትያ ሰዎችን ከአይሁድ ህይማኖተኞች መረብ ለማዳን በመጻፍ ለሰላም ሁለት መንገዶች እንዳሉ ሁሉ በማጠቃለያ ጽሁፉ ጳውሎስ "ሰላምና ምህረት ወንጌልን በምትከተሉ ሁሉ ላይ ይሁን" እና "ሰላምና ምህረት እስራኤላዊ ለሆነ ሁሉ" ቢል ኖሮ ለማድረግ የሞከረውን ነገር ሁሉ ያበላሻል።

3.ወንጌልን በተመለከተ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ "አይሁድ የለም ግሪክ የለም" በማለት ጽፎአል። የክርስቶስ የሆነ ሁሉ የአብርሀም ዘር ነው 3፡28-29።

4. "እና" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል እዚህጋ በብዙ መንገዶች ሊተረጎም ይችላል፣ብዙውን ጊዜ "እንኳን" ተብሎ ተተርጉሟል ደግሞም ገለጻን ይጀምራል። በዚህ መንገድ ነው እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው፤ "በዚህ ህግ ለሚሄዱ ሁሉ፣ ሰላም እና ምህረት በነርሱ ላይ ይሁን፣ ደግሞም (ይሽውም)፣ በእግዚአብሄር እስራኤልም ላይ።"

ማጠቃለያው

3 ለቁ 17 የገላትያ ሰዎች ለደብዳቤው በሚገባ ምላሽ እንደሚሰጡ ደግሞም ለእነርሱ ያለ ጭንቀቱን እንደሚያቆሙለት ጳውሎስ ተስፋ ያደርጋል።

29 የገላትያ ክርስቲያኖች በሀሰት አስተማሪዎች መወሰድ ምክንያት ጳውሎስ በታላቅ ሀዘን ውስጥ ነበር (1፡6፣ 3፤1፣ 4፡16-20)።

በቁ 17 ላለው ንግግሩ የገላትያ ሰዎች ምን ተሰምቶአቸዋል ብለህ ታስባለህ?

1)በጣም እንዲያዝን ስላደረጉት አዝነው ሊሆን ይችላል

2) ለወንጌል ታማኝ በመሆን ጳውሎስ በሰውነቱ ላይ ካለው የስደት የጎሉ ጠባሳዎ ጋር ሲነጻጸር ለወንጌል ጻማኝ ባለመሆን በሰውነታቸው ላይ ስላለው የመቀደድ ምልክቶች አፍረው ሊሆን ይችላል በተለይም እርሱ ላይ የነበሩት የመከራ ጠባሳዎች የተተለተሉት እነርሱን ባሳቱአቸው ሰዎች የመጡ ስለነበሩ።

3ሐ. ቁ 18 ቡራኬ

30.ለዚህ አስቸጋሪ ደብዳቤ በምን መንገድ ነው ይህ ጸሎት ፍጹም ፍጻሜ የሚሆነው?

በአራት መንገድ ትክክለኛ ፍጻሜ ነው፡

1. *"ጸጋ . . .ከናንተ ጋር ይሁን . . ." ለነርሱ የሚያቋርጠውን የፍቅርና የህይወት መፍሰስ ያስታውሳቸዋል።*
2. *"ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ" የሚለው መጠሪያ ስለ ኢየሱስ አምላክነት፣ ሰውነት እና ስለ ነብይ፣ ካህንና ንጉስ አገልግሎቱ ያስታውሳቸዋል።*
3. *"በመንፈሳችሁ" የደህንነት በረከቶች አሁን አካላዊ ሳይሆኑ መንፈሳዊ መሆኑን ያስታውሳቸዋል። የክርስቲያን እምነት በልብ ውስጥ እንጂ በአካላዊ ስርአቶች አይደለም።*
4. *"ወንድሞች" እንደተወደዱ አንድ ቤተሰብ አባላት የጳውሎስን ክርስቲያናዊ ፍቅር ያረጋግጣል።*